# በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡

# ዋጋ ፡ ስለሌላቸውና ፡ ፈራሽ ፡ ጋብቻዎች ፡

ከሚስስ ፡ ካተሪን ፡ አዶኖቫን*

## I

## መግቢያ ።

ዋጋ ፡ በሌለውና ፡ ሊፈርስ ፡ በሚችለው ፡ ጋብቻ ፡ መሃከል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ልዩነት ፡ አለ ፡ ወይ?

እንደ ፡ ጸሐፊው ፡ አባባል ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ጉድለቶች ፡[1] በሚያወሳበት ፡ ጊዜ ፡ በተለየ ፡ መደባቸውን ፡ ጠቅሶ ፡ የሚያብራራው ፡ ሊፈርሱ ፡ ስለ ሚችሉት ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነቶች ፡ ብቻ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመው ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነት ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ያልተ ጠቀሰ ፡ ቢሆንም ፡ ከሕጉ ፡ ጋር ፡ አዋህዶ ፡ ሕጉ ፡ ላልጠቀሳቸው ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳዮች ፡ መፍትሔ ፡ ሊያስገኝ ፡ የሚችል ፡ በመሆኑ ፡ ጠቃሚነቱ ፡ በቀላሉ ፡ ሊገመት ፡ የሚቻል ፡ አይደለም ።

"ዋጋ ፡ የሌለው" ፡ እና ፡ "ሊፈርስ ፡ የሚችለው" ፡ የሚባሉት ፡ ቃላት ፡ በኮሞን ፡ ሎው ፡ ምድብ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ። ተቃራኒዎቻቸውም ፡ በኮንቲኔንታል ፡ የአውሮጳ ፡ አህጉሮች ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ አሉ ። እነዚህ ፡ ሁለት ፡ የሕግ ፡ ምድቦች ፡ የተስተካከለ ፡ የምርጥ ፡ ቃላት ፡ አሰካክ ፡ ስለሚያንስባቸው ፡ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ ቃላትን ፡ ለማዳቀል ፡ በፍጹም ፡ አይችልም ። በአማርኛው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ "ዋጋ ፡ የሌ ለው ፡" ወይም ፡ "ሊፈርስ ፡ የሚችል ፡" ተብለው ፡ ለሚጠሩት ፡ ቃላት ፡ ደንበኛ ፡ ለያንዳ ንዳቸው ፡ የሚሆኑ ፡ የአንድ ፡ ቃል ፡ ትርጉም ፡ የላቸውም ።[2] ሆኖም ፡ ሁለቱ ፡ ባላቸው ፡

---

* በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ረዳት ፡ ፕሮፌሰር ። ጸሐፊዋ ፡ ከሚስተር ፡ ዊንሺፕና ፡ ከፕሮፌሰር ፡ ጆርጅ ፡ ቺቹኖቪች ፡ ስላገኘችው ፡ ጠቃሚ ፡ ትችትና ፡ ሐተታ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ልትጠቅስ ፡ ትወዳለች ።

1. ጉድለት ፡ ኖሯቸውና ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ሊፈርሱ ፡ የሚችሉ ፡ ጋብቻዎች ፡ "ሊፈርሱ ፡ የሚችሉ ፡" ተብለው ፡ መጠራት ፡ ይኖርባቸዋል ፡ የሚል ፡ ተቃውሞ ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ጋብቻዎች ፡ በሙሉ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፰፻፰ ፡ መሠረት ፡ በሞት ፣ በፍቺ ፡ ወይም ፡ ጉድለት ፡ በመ ኖሩ ፡ ሊፈርሱ ፡ የሚችሉ ፡ ናቸው ።

2. የትክክለኛው ፡ ቃል ፡ አሰጣጥ ፡ ዘዴ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። በፈረንሣይኛ ፡ የተጻፈው ፡ የኢትዮ ጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከአማርኛውና ፡ ከእንግሊዝኛው ፡ ግልባጮች ፡ በዚሁ ፡ ረገድ ፡ በጣም ፡ የተሻሻለ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። ስለዚህም ፡ አንዳንዴ ፡ የእንግሊዝኛውና ፡ የአማርኛው ፡ ግልባጮች ፡ ሊረዱን ፡ እንደማይችሉ ፡ በዚሁ ፡ አባባል ፡ ልንገነዘበው ፡ እንችላለን ። በፈረንሣይኛ ፡ የተጻፈው ፡ አንዳንድ ፡ ድርጊቶችን ፡ "Sans valeur au regard de la Loi civile," በሚላቸው ፡ ጊዜ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ትርጉም ፡ "of no effect under the civil Law" ይላቸውና ፡ የአማርኛ ውም ፡ ደግሞ ፡ "ዋጋ ፡ የሌለው ፡" ወይም ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸው ፡ ድርጊቶች ፡ ይላቸዋል ። (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ ና ፡ ፵፩) ። በሌላ ፡ ቦታም ፡ የፈረንሣይ ፡ አንዱን ፡ ድርጊት ፡ "nul" ነው ፡ ሲል ፡ የእንግሊዝኛው ፡ እንደ ፡ ዱሮው ፡ "of no effect" ይለዋል ። የአማርኛው ፡ ግን ፡ "ፈራሽ፡" የሚል ፡ የተለየ ፡ ስያሜ ፡ ይሰጠዋል ። (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፲፫ ፤ ፫፻፹፯ ፤ ፲፻፴፮ ፡ (፪) ፤ ፲፻፵ ፡ (፫) እና ፡ ፲፻፴፰) ።

ስነ ፡ ሐሣብ ፡ መሠረት ፡ ሕጉን ፡ ለመግለጽ ፡ በቂ ፡ ሆነው ፡ ከመ፤ኘታቸውም ፡ በላይ ፡ ካለነሱ ፡ በስተቀር ፡ ሌሎች ፡ ቃሎች ፡ ባለመኖራቸው ፡ በነዚሁ ፡ ቃላት ፡ መጠቀሙ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በሚቀርበው ፡ ሐሳብ ፡ ለመረዳት ፡ ይቻላል ።

ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ተግባር ፡ ባዶ ፡ ተግባር ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ይህም ፡ የሆነ በት ፡ ምክንያት ፡ ተግባሩ ፡ ሊፈጽመው ፡ የተነሳሳውን ፡ ነገር ፡ ሳይሳካ ፡ ሲቀርና ፡ እንዲሁም ፡ በተግባሩ ፡ መሠረት ፡ ሊገኝ ፡ የታቀደውን ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ ሳይገኝ ፡ ሲቀር ፡ ነው ። "Qvod nullum est, nullum producit effectum"[3] አንድ ፡ ድርጊት ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራበት ፡ ጊዜ፡ ጉድለቱ ፡ ጥልቅ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሳ ፡ የድርጊቱ ፡ ህላዌ ፡ የሚያጠፋ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ። "ማንኛውም ፡ ሕጋዊ ፡ ድርጊት ፡ ጉድለት ፡ ካለበት ፡ ጉድለቱ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ወይም ፡ ፈራሽ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ። ድርጊቱ ፡ መጀመሪያውኑ ፡ በተወጠነው ፡ ሐሳብ ፡ መሠረት ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ ካላስገኘ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ተግባር ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።"[4] በተለመደው ፡ አስተሳሰብ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ድርጊት ፡ ዋጋ ፡ የለውም ፡ የሚባለው ፡ የተጠበቀው ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ በማይኖርበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ይህ ፡ አስተሳሰብ ፡ ሁልጊዜ ፡ ሊሆን ፡ አለመቻሉን ፡ የሚገልጽ ፡ ከብዙዎቹ ምሳሌዎች ፡ አንዱ ፡ የወንጀለኞች ፡ መከሰስ ፡ ጉዳይ ፡ መጥቀስ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ዋናው ፡ ሐሳብ ፡ ከላይ ፡ እንዲተገለጸው ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ድርጊት ፡ ዋጋ ፡ የለውም ፡ ብለን፡ ለማለት ፡ የምንችለው ፡ ድርጊቱ ፡ የተጠበቀበትን ፡ ያህል ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ ሳያስ ገኝ ፡ ሲቀር ፡ ነው ።

ሊፈርስ ፡ የሚችል ፡ ብለን ፡ የምንጠራው ፡ ተግባር ፡ ደግሞ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ጉድለት ፡ ቢኖርበት ፡ ያው ፡ የተጠበቀበትን ፡ ያህል ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ ሲያስገኝ ፡ ነው ። በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ ድርጊት ፡ የሚገኘው ፡ ጉድለት ፡ ከባድ ፡ ካለመሆኑ ፡ የተነሳ ፡ ተግባሩ ፡ የተጠበቀበትን ፡ ያህል ፡ ውጤት ፡ ከማስገኘት ፡ ሊከለክ ለው ፡ አይችልም ።

---

"nul" የሚለውን ፡ የፈረንሣይኛ ፡ ቃል ፡ በእንግሊዝኛና ፡ አማርኛ ፡ ሲተረጎም ፡ "null" እና ፡ "ፈራሽ ፡" ወይም ፡ "የማይጸና ፡" ይባላል ። (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፯፻፯) ።

"la nullite" በአንቀጽ ፡ ፫፻፲፬(፪) እና ፡ ፫፻፳፱(፫) ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ሲተረጎም ፡ "nullity" ይሆናል ፡ ወደ ፡ አርማኛ ፡ ሲተረጎምም ፡ ደግሞ ፡ "ፈራሽ" ይባላል ።

"L'annulation" ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ሲተረጎም ፡ "the annulment" ተብሎአል ፡ በአማርኛው ፡ ደግሞ ፡ በንኡስ ፡ ቁጥር ፡ አንድ ፡ "መፍረስ ፡" ሲሆን ፡ በንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ሁለትና ፡ ሦስት ፡ ደግሞ ፡ "መሻር" ተብሎአል ።

ሕጉ ፡ ስለ ፡ ውል ፡ በሚያወሳበት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ "annulé," "annulation" እና ፡ "nullite" እንደ ፡ "invalidated" ወይም ፡ "invalidation" ሆነው ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ሲተረጎም ፡ በአማር ኛ ፡ ደግሞ ፡ "ፈረሰ" ፡ ወይም ፡ "መፍረስ" ፡ የሚል ፡ ስያሜ ፡ ተሰጥቶአቸዋል ፡ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ሺ፯፻፺፰ ፡ ና ፩ሺ፯፻፺፱) በአንቀጽ ፡ ፩ሺ፯፻ ፡ ትርጉሙ ፡ "ቀረ ፡" ወይም ፡ "መቅረት ፡" ነው ። በአንቀጽ ፡ ፩ሺ፯፻፰ ፡ "መቅረት" ፡ እና ፡ መፍረስ ፡ ነው ። በ፩ሺ፰፻፰ ፡ "ፈረሰ" ፡ እና ፡ "ሰረዘ" ሲሆን ፡ በ፩ሺ፰፻፱ ፡ "መርጋት ፡" ሆኖ ፡ በ፩ሺ፰፻፲ ፡ ደግሞ ፡ "መሰረዝ ፡" ሆኖአል ።

ደራሲው ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ ተክለአብ ፡ ያደረጉላቸውን ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ የአማርኛ ፡ ቃላት ፡ ገለጻ ፡ እዚሁ ፡ ለማውሳት ፡ ይወዳሉ ።

3. ጂ. ሪፐርት ፡ ኤንድ ፡ ጂ. ቡላንጀር ፡ ትሬይት ፡ ደ ፡ ድርዋ ፡ ሲቪል ፡ ፓሪስ ፡ ላይቢሬር ፡ ዠኔራል ፡ ደ. ድርዋ ፡ ኤ ፡ ደ ፡ ጁሪስ ፡ ፕሩደንስ ፡ ፲፱፻፶፮ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ቁ. ፩ሺ፫፻፺፱ ።

4. ጂ. ደብሊው ፡ ፓተን ፡ ጁሪስፕሩደንስ ፡ (3ኛ ፡ እትም ፡ በዴ. ፒ. ዴርሃን) ፡ (ኦክስፎርድ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ፕሬስ ፡ ፲፱፻፷፬) ፡ ገጽ ፡ ፬፻፹፩ ።

“በታሰበው ፡ የመጀመሪያ ፡ ዓላማ ፡ ተመርቶ ፡ ውጤት ፡ የማይሰጥና ፡ የማ ይሠራ ፡ ነገር፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ። ውጤት ፡ ኖሮት ፡ ውጤቱ ፡ ጉድለት፡ ቢኖርበት ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ለመሥራቱ ፡ ጥርጥር ፡ ባይኖረውም ፡ ወገኖ ቹ ፡ እንዳይሠራ ፡ ለማድረግ ፡ የሚያስችል ፡ የማፍረስ ፡ መብት ፡ አላቸው ።”[5]

በፈራሽ ፡ ተግባር ፡ የሚገኘው ፡ ጉድለት ፡ በመጠኑ ፡ ከበድ ፡ ያለ ፡ በመሆኑ ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ጉድለቱን ፡ ጠቅሶ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አማካይነት ፡ ሊያፈርሰው ፡ ይችላል ። ድርጊቱ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ካልተወገደ ፡ ሕጋዊ ፡ ተግባር ፡ ሆኖ ፡ ሊሠራበት ፡ ይቻላል ።[6] ከአዋቂዎቹ ፡ ጸሐፊዎች ፡ አንድ ፡ ሊፈርስ ፡ ስለሚችለው ፡ ተግባር ፡ አስተያየታቸውን ፡ ሲሰጡ ፡ ትክክለኛውን ፡ የመመሪያ ፡ ዘዴ ፡ ተግባሩ ፡ የተውጠነጠነውን ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ ያስገኛል ፡ ማለቱ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ውጤቱ ፡ ሊፈርስ ፡ የሚችለው ፡ ድርጊቱ ፡ ራሱ ፡ ከወገኖቹ ፡ መሃል ፡ ለአንዱ ፡ በሚሰጠው ፡ የማፍረሻ ፡ መብትም ፡ ጭምር ፡ ነው ።[7]

ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ጋብቻ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ቢኖር ፤ ከሠርጉ ፡ በዓል ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ከዛ ፡ በኋላ ፡ በሚኖርበት ፡ ጠለቅ ፡ ያለ ፡ ጉድለት ፡ ምክንያት ፡ እንዳልተቋቋመ ፡ ከመቆጠሩም ፡ ሌላ ፡ የተጎዱት ፡ ወይም ፡ የሚያገባቸው ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ በዚሁ ፡ አኳኋን ፡ ሊሠሩበት ፡ ይችላሉ ። ማንኛውም ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ መግለጫ፡ ጋብቻው ፡ እንዳልነበረ ፡ እንዲቆጠር ፡ ለሚለው ፡ ውሳኔ ፡ ለማጽደቅና ፡ የወገኖቹን ፡ አኳኋን ፡ እንዳልተጋቡ ፡ የሚቆጠር ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ብቻ ፡ የተመደበ ፡ ነው ።[8] ያገባኛል ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ቢሞቱም ፡ ጋብቻው ፡ እንዳልነበረ ፡ እንዲቆጠር ፡ ለማድረግ ፡ ማመልከቻ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ። ወገኖቹ ፡ ሕጋዊ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ካለመሆናቸው ፡ የተነሳ ፡ የተለመደው ፡ በሕጉ ፡ የሚሰጠው ፡ የጋብቻ ፡ ውጤት ፡ አያገኙም ። ለምሳሌ ፡ ያሀል ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ስለማይ ኖራቸው ፡ አንዱ ፡ በሚሞትበም ፡ ጊዜ ፡ የቀረው ፡ የሟቹን ፡ ንብረት ፡ ለመውረስ ፡ አይችልም ። ከዋጋ ፡ የሌለው ፡ ጋብቻ ፡ በፊት ፡ የሚደረገው ፡ ማንኛውም ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ከንቱ ፡ ነው ። ሚስቲቱ ፡ እንደዱሮዋ ፡ የነበራትን ፡ መኖሪያ ፡ ትይዛለች ። ከዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻ ፡ የሚወለዱት ፡ ሁሉ ፡ የጋብቻው ፡ ልጆች ፡ አይደሉም ። ሆኖም ፡ የወለ ዱዋቸው ፡ ሰዎች ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ስለነበራቸው ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ልጆቻቸው ፡ መሆናቸውን ፡ ያለአንዳች ፡ ጥርጥር ፡ ሊያረጋግጡ ፡ ይችሉ ። እንዲዚሁ ፡ ዓይነት ፡ አከራካሪ ፡ ነገር ፡ ሲነሳ ፡ በዋጋ ፡ የሌለው ፡ ጋብቻ ፡ በኩል ፡ ያሉት፡ የሚያገባቸው ፡ ወገኖች ፡ በሙሉ ፡ ሊጠቀሙበት ፡ የሚችሉት ፡ ይህንን ፡ ደንበኛ ፡ መከላከያ ፡ ነው ።

ሊፈርስ ፡ የሚችለውና ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ የሚባሉት ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነቶች ፡ በጣም ፡ የተለያዩ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ። አንድ ፡ ጋብቻ ፡ ጸንቶ ፡ ዘላቂነትን ፡ የሚያስገኘው ፡

---

5. ኤፍ ፡ ፓሉክ ፤ ጁሪስፕሩደንስ ፡ ኤንድ ፡ ኤሲይስ ፤ (ለንደን ፤ ማክሚላን ፤ ፲፱፻፷፩) ፡ ገጽ ፡ ፹፱ ።

6. ለምሳሌ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፫፻፲፫ ፡ እና ፡ ፫፻፲፬ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ከሥ ልጣኑ ፡ በላይ ፡ የፈጸማቸውን ፡ ሥራዎች ፡ እንዲፈርሱ ፡ የመጠየቂያ ፡ መብት ፡ ለአካለመጠን ፡ ላላደረ ሰው ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ ለእንደራሴዎች ፡ ይሰጣሉ ። አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ተግባሩን ፡ ካላፈረ ሰው ፡ ጽኑ ፡ ሆኖ ፡ ይቀራል ።

7. ኤፍ. ኤች. ኔዎርክ ፤ “ዘ ፡ አፕሬሽን ፡ አፍ ፡ ነሊቲ ፡ ዲክሪስ ፤” ሞደርን ፡ ሎው ፡ ሪቪው ፤ ቮልዩም ፡ ፳ (፲፱፻፶፰) ገጽ ፡ ፪፻፫ በገጽ ፡ ፪፻፭ ።

8. የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፳፬ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ “የጋብቻ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ ውል ፡ የተፈ ጸመ ፡ ለመሆኑና ፡ ይህም ፡ ጋብቻ ፡ የሚጸና ፡ መሆኑን ፡ ለመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸውም ፡ ዳኞች ፡ ብቻ፡ ናቸው ።” ይህ ፡ አባባል ፡ የሚያሳየው ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ እንዲብራራ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መላክ ፡ እንዳለበት ፡ ነው ።

9. ጋብቻም ፡ ባይኖር ፡ አጠራጣሪ ፡ ሁኔታ ፡ ቢገኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሁኔታውን ፡ አጥንቶ ፡ ለማብራራት ፡ ቢፈቅድለት ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ጂ. ሪፐርት ፡ ኤንድ ፡ ጂ ፡ ቡላንጀር ፤ ከላይ ፤ በማስታወሻ ፡ ፫ ፤ የተጠቀሰ ፡ ቮል ዩም ፡ ፩ ቁ. ፩ሺ፫፻፲፱ ።

በማይወቀስበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። በውጤቱ ፡ በኩል ፡ የታየ ፡ እንደሆነ ፡ ሁለት ፡ የተለያዩ ፡ ነገሮችን ፡ ማውሳቱ ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ይኸውም ፡ አንደኛ ፡ ጋብቻው ፡ ሊፈርስ ፡ የሚችል ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ባለመወቀሱ ፡ ምክንያት ፡[10] የማይከለከል ፡ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ የሚከለከል ፡ ሲሆን ፡ ነው ። በመጀመሪያው ፡ አኳኋን ፡ ጋብቻው ፡ ጸንቶ ፡ የተለመዱት ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤቶችን ፡ ያስከትላል ። በሁለተኛው ፡ አኳኋን ፡ ግን ፡ እስከተከለከሉ ፡ ድረስ ፡ ዋጋ ፡ በሚሰጣቸው ፡ ጋብቻዎችና ፡ ከመጀመሪያ ውኑ ፡ ዋጋ ፡ የላቸውም ፡ በሚባሉት ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነቶች ፡ ተጨማሪ ፡ ልዩነት ፡ እንዳለ ፡ ማወቁ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። "ሊፈርስ ፡ የሚችል ፡" የሚለውን ፡ ቃል ፡ በጥቅም ፡ በኩል ፡ ለማተት ፡ የማቻለውም ፡ እዚሁ ፡ ላይ ፡ ነው ። ቃሉን ፡ ለሚመለከተው ፡ ሁሉ ፡ ሊፈርስ ፡ የሚችል ፡ ሲባል ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ሆኖ ፡ ይታየዋል ። ቃሉ ፡ በሚከተሉት ፡ ሐሣቦች ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ በፍጹም ፡ አያሳይም ። ይኸውም ፡ አንድ ፡ ድርጊት ፡ ከመጀመሪያውኑ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ሳይሆን ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በኩል ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ ሲገለጽና ፤ እንዲሁም ፡ በውሳኔው ፡ መሠረት ፡ ለመጪው ፡ ጊዜ ፡ የማይሠራበት ፡ ሲደረግ ፡ እስከተከለከለበት ፡ ጊዜ ፡ የነበሩትን ፡ ውጤቶች ፡ ግን ፡ ቋሚነታቸው ፡ በሕግ ፡ ታውቆ ፡ እንደሚሠራባቸው ፡ ስለመታወቁ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ።[11]

እዚሁ ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ ክፍሎች ፡ ይመነጫሉ ። እነሱም ፤ አንደኛው ፡ ከመጀመሪያው ፡ ጀምሮ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ይህም ፡ ማለት ፡ ነገሩ ፡ እንዳልነበረ ፡ ወይም ፡ ውጤት ፡ እንዳልሰጠ ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፤ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ መቋቋሙ ፡ ቢታወቅም ፡ ቅሉ ፡ ጉድለቱ ፡ በመገኘቱ ፡ የነበረውና ፡ ያለው ፡ እንዲሁም ፡ ለመጪው ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጠው ፡ ውጤት ፡ ሲከለከል ፡ ነው ። ሦስተኛውና ፡ የመጨረሻው ፡ ደግሞ ፡ ለመጪው ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ውጤት ፡ እንዳይሰጥ ፡ የተከለከለ ፡ ሆኖ ፡ ከተከለከለበት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡ ውጤቶች ፡ በሙሉ ፡ የማይነኩ ፡ ሲሆን ፡ ነው ። (void exnunc) የኢትዮጵያ ፡ ጋብቻ ፡ ሕግ ፡ በዚሁ ፡ በሦስተኛው ፡ ክፍል ፡ ይመደባል ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ጉድለቶች ፡ በሚያወሳበት ፡ ጊዜ ፡ "nullity" የሚለውን ፡ ቃል ፡ በሦስተኛው ፡ ክፍል ፡ ለተመደበው ፡ ሐሳብ ፡ ሊመጥቅስ ፡ አይጠቀምበትም ።[12] የጋብቻ ፡ ጉድለት ፡ ከሞትና ፡ ከፍቺ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ የመፋታት ፡ ደምበኛ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ።[13] በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ "የመፋታት ፡ ጥያቄ" ፡ የሚያቀርበው ፡ የሚለው ፡ አባባል ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የጋብቻ ፡ ሁኔታዎች ፡ ባለመጠበቃቸው ፡ የሚወሰን ፡[14] ሲሆን ፡ በዘልማድ ፡ በኩል ፡ የታየ ፡

10. ሊፈርስ ፡ የሚችለውን ፡ ጋብቻ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለመከራከር ፡ የሚችሉት ፡ የቅርብ ፡ ባለጉዳዮች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። መብት ፡ ያለው ፡ ማነው ፡ የሚለው ፡ ሐተታ ፡ በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ "nullite absolue" እና ፡ "nullite relative" የተባሉትን ፡ ሁለት ፡ የተለያዩ ፡ ነገሮችን ፡ ይፈጥራል ። የዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ ጉድለቱ ፡ ጠለቅ ፡ ያለ ፡ ካለመሆኑ ፡ የተነሳ ፡ የማፍረሱ ፡ መብት ፡ ለጋብቻው ፡ ቅርብ ፡ ወገኖች ፡ ብቻ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

11. ስለ ፡ ዋጋ ፡ የሌልውና ፡ ሊፈርስ ፡ የሚችለው ፡ ጋብቻ ፡ የሚጽፉት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ የቃል ፡ አቋም ፡ አለመኖሩን ፡ ያውቃሉ ። ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ፯ የተጠቀሰው ፡ ኔወርክንና ፡ ሴትኢ ፤ በኤም ፡ ኤል ፡ አር ፤ ቮልዩም ፡ ፲፩ (፲፱፻፵፰) ገጽ ፡ ፲፯ ፡ ላይ ፡ የጻፈውን ፡ ደብዳቤ ፡ ተመልከት ። በተጨማሪም ፡ ዲ. ላሶክ ፤ ዲ. "አፕሮቢሽን ፡ አፍ ፡ ማሪኤጅ ፡ ኢን ፡ ኢንግሊሽ ፡ ሎው ፡ ኤንድ ፡ ዘ ፡ ዶክትሪን ፡ አፍ ፡ ቫሊዴሽን" ፤ በሚለው ፡ ላይ ፡ የሰጠውን ፡ አስተያየት ፡ ተመልከት ፤ ሞዶርን ፡ ሎው ፡ ሪቪው ፤ ቮልዩም ፡ ፳፯ (፲፱፻፷፫) ፡ ገጽ ፡ ፩፻፵፱ ።

12. ከዚህ ፡ የሚለዩት ፡ ደግሞ ፡ አንዳንድ ፡ አንቀጾች ፡ አሉ ። እነሱም ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፴፱(፫) ፤ አንቀጽ ፡ ፮፻፯ ፡ እና ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፳፫ ፡ ናቸው ። አንቀጽ ፡ ፫፻፴፱ (፫) ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ በሚያወሳበት ፡ ጊዜ ፡ (nullity) ሲያስገባ ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፯ ፡ ደግሞ ፡ በ(null) ሲጠቀም ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፳፫ ፡ ስለ ፡ ሐይማኖት ፡ ጋብቻ ፡ በሚያወራበት ፡ ጊዜ ፡ የሐይማኖት ፡ መሪዎች ፡ ጋብቻውን ፡ annul ያደርጉታል ፡ ስለሚል ፡ "annulment" በሚለው ፡ ቃል ፡ ይጠቀማል ፡ ማለት ፡ ነው ።

13. የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፷፫ ።

14. የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፷፫(፪) ።

እንደሆነ ፡ ፈራሽ ፡ የምትለውን ፡ ቃል ፡ ወክሎ ፡ ይገኛል ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቃላት ፡ ይዞታ ፡ በዚሁ ፡ ረገድ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። የጉድለት ፡ ያለባቸው ፡ ጋብቻዎች ፡ መፍረስና ፡ የመፋታት ፡ ውጤት ፡ በጣም ፡ የተቀራረበ ፡ ነው ።[15] ጠቃሚነቱ ፡ እንግዲህ ፡ በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ "nullité" ከሚለው ፡ ቃል ፡ ለሚነሳው ፡ ፕሮብሌም ፡ መፍትሔ ፡ በመስጠቱ ፡ ነው ። ሪፐርት ፡ እና ፡ ቡላንጀር ፡ ሲናገሩ ፤

> "ማንኛውም ፡ ጋብቻ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ ከተባለ ፡ እንዳልነበረ ፡ ስለሚቆጠር ፡ የነበረውና ፡ አሁንም ፡ ያስገኘው ፡ ውጤት ፡ ውድቅ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ለወደፊቱ ፡ በፍጹም ፡ ሊሠራበት ፡ አይቻልም ። ዋጋ ፡ ያለው ፡ ያስመሰለው ፡ የጋብቻ ፡ ስነ ፡ ሥርዓት ፡ ቢከናወንም ፡ ጋብቻው ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ መግለጫ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ ከተባለ ፡ ያው ፡ መሰረዙ ፡ ነው ። Quod nullum est nullum producit effectum[16]

የፈረንሣይ ፡ሕግ ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ የተመደበ ፡ ይመስላል ። ከዚሁ ፡ ለሚነሳው ፡ ፕሮብሌም ፡ ለማቃለል ፡ (putative theory) ፒዩቴቲቭ ፡ ቲዮሪ ፡ የሚለውን ፡ አስተሳሰብ ፡ በማስገባት ፡ በታማኝነት ፡ ለሚጋቡት ፡ ሁሉ ፡ እንዲያገለግላቸው ፡ ተደርጓል ። የዚሁ ፡ ሐሳብ ፡ ውጥን ፡ ባለማወቅና ፡ በንጹሕ ፡ ልቦና ፡ ለተከናወኑት ፡ ጋብቻዎች ፡ ከላይ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ (void exnunc) ለማድረግ ፡ ሲሆን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ልቦናና ፡ የማወቅ ፡ ችሎታ ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ እንደሚረዳ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይህን ፡ ዓይነት ፡ ስነ ፡ ሐሳብ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ አያስፈልግም ። የሕጉ ፡ አዘጋጆች ፡ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ችግር ፡ የሚፈጥር ፡ ስነ ፡ ሐሳብ ፡ እንዲወገድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ theory of nullity of marriages የሚለውን ፡ ስነ ፡ ሐሳብ ፡ ደግሞ ፡ በሙሉ ፡ እንዳይገባ ፡ ወስነዋል ። አዘጋጆዎቹ ፡ ይኸንን ፡ ነገር ፡ ያስገባን ፡ እንደሆነ ፡ ችግር ፡ ይፈጥርብናል ፡ እና ፡ ደግሞ ፡ ጠቃሚነቱ ፡ ይኸን ፡ ያኸል ፡ አለመሆኑ ፡ በመገንዘብ ፡ ብንተወው ፡ ይሻላል ፡ ብለዋል ። በቅን ፡ ልቦናና ፡ ባለማወቅ ፡ የተከናወነው ፡ ጋብቻ ፡ ለማስወገድ ፡ የምንችለው ፡ ስለ ፡ ናሊቲ ፡ (nullity) ሳይሆን ፡ ስለ ፡ (dissolution) በምናወራበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።[17] በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የቅን ፡ ልቦና ፡ አሠራር ፡ ጠቃሚነቱ ፡ የፈረሰው ፡ ጋብቻ ፡ ይሠራበት ፡ ይሆን ፡ በሚል ፡ አስተሳሰብ ፡ ሳይሆን ፡ የመፍረሱ ፡ አኳኋን ፡ ወይም ፡ ውጤት ፡ እንዴት ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ ለመገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ነው ።[18]

## II

## <u>የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከመጀመሪያው ፡ ፍርስ ፡ በሆኑ ፡ ጋብቻዎች ፡ ላይ ።</u>

በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ የሚገኙት ፡ ውድቅ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ፡ የምንላቸው ፡ ጋብቻዎች ፡ (እንቅፋት) ፡ መሰናክል ፡ ኖሯቸው ፡ መሰናክሉ ፡ እንደምንም፡

---

15. በአንቀጽ ፡ ፻፺፯ (፩) መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጉድለት ፡ ያለበት ፡ ጋብቻ ፡ ሲያፈርስ ፡ ፍቺን ፡ የሚመለከቱትን ፡ ሕጎች ፡ ተከትሎ ፡ መሥራት ፡ ይኖርበታል ።

16. ጂ. ሪፖርት ፡ ኤንድ ፡ ጂ. ቡላንጀር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ 3 የተጠቀሰውን ፡ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ቁ. ፩ሺ፫፻፷፱ ተመልከት ።

17. አር ፡ ዴቪድ ፤ ለ ፡ ድርዋ ፡ ደ ፡ ላ ፡ ፋሚል ፡ ዶን ፡ ለ ፡ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ኢትዮፒ ፤ (ሚላኖ ፡ ጂኡፍሬ ፤ ፲፱፻፷፯) ፤ ገጽ ፡ ፶፯ ። የፈረንሣዩ ፡ ጽሑፍ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ የተተረጐመው ፡ በደራሲው ፡ ነው ።

18. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፻፺፯ (፫) ።

ሳይቆጠር ፡ የሠርጉ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተግባደደ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። የዚሁ ፡ ዓይነት መሰናክሎች ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ውስጥም ፡ ይገኛሉ ። እነሱም ፡ በዱሮው ፡ ጓደኝነ ትና ፡ ጋብቻ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በዕድሜ ፡ ምክንያት ፡ የሚመጡ ፡ ናቸው ። በተጨማ ሪም ፡ ከሠርጉ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚመነጩት ፡ ጉድለቶች ፡ ይገኙባቸዋል ።[19] በዱ ሮው ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻዎች ፡ የተከለከሉ ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፡ በወንጀል ፡ ቅምር ፡ ያስቀጡ ፡ ነበር ።[20] በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ የጋብቻ ፡ መሰናክሎች ፡ በብዛት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ገብተዋል ።[21] ሃይማኖትን ፡ የሚነኩ ፡ ግን ፡ በሙሉ ፡ ቀርተዋል ።[22]

የጋብቻ ፡ (እንቅፋቶች) ፡ መሰናክሎች ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩት ፡ ነገሮች ፡ በፍትሐ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በሦስት ፡ መደቦች ፡ ተከፍለው ፡ እናገኛቸዋለን ። አንደኛው ፡ ለሠርጉ ፡ የአከባበር ፡ በዓል ፡ መሰናክል ፡ ከመሆን ፡ በስተቀር ፡ ቀጥሎ ፡ ላለው ፡ ጊዜ ፡ የጋብቻውን ፡ ቋሚነት ፡ ፈጽሞ ፡ የማይነካ ፡ ሲሆን ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ መሰናክሉ ፡ በዓሉን ፡ ለማደናቀፍ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚሠራበት ። በዚሁ ፡ አኳኋን ፡ የሚከናወኑት ፡ ጋብቻዎች ፡ ሁለት ፡ ናቸው ። አንደኛው ፡ የጋብቻው ፡ ተቃዋሚ ፡ ሲኖር ፡ ሲሆን ፡[23] ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ በሕጉ ፡ የተወሰነው ፡ የባልቴትነት ፡ ጊዜ ፡ ሳያልቅ ፡ ጋብቻው ፡ የተገባደደ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።[24] በሁለቱም ፡ ሁኔታዎች ፡ ጋብቻው ፡ መከልከል ፡ ይኖርበታል ። ሳይከለከል ፡ ሲቀር ፡ ግን ፡ ቋሚ ፡ ይሆናል ።[25] በዚሁ ፡ አኳኋን ፡ ጋብ ቻው ፡ እንዲመሠረት ፡ የረዳ ፡ ሐላፊነት ፡ ያለው ፡ ሰው ፤ ተጋቢዎቹና ፡ የሚያጋቡዋ ቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በወንጀል ፡ መቀጣት ፡ ይኖርባቸዋል ።[26] ጋብቻው ፡ ግን ፡ በምንም ፡ ምክንያት ፡ ሊወድቅ ፡ አይችልም ። የሠርጉ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ የጋ ብቻው ፡ ቋሚነት ፡ የማያጠራጥር ፡ ይሆናል ።

በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ የተመደቡት ፡ የጋብቻ ፡ መሰናክሎች ፡ የሠርጉ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንዳይከናወን ፡ ለመከልከል ፡ ከመቻላቸውም ፡ በላይ ፡ ምናልባት ፡ የተከና ወነ ፡ እንደሆነም ፡ ጋብቻውን ፡ ሊያፈርሱት ፡ የሚችሉ ፡[27] ሲሆን ፡ ነው ። የዚህ ፡

---

19. ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ (የተተረጎመው ፡ በአባ ፡ ጳውሎስ ፡ ጻዲ ፡ ፲፱፻፷፭) ፡ ገጽ ፡ ፻፴፱ — ፻፵፬ ። መሰናክ ሎቹ ፡ በሙሉ ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፤ በሥጋ ፡ ወይም ፡ በጋብቻ ፡ ዝምድና ፤ ሌሎችም ፡ ዓይነት ፡ ዝም ድናዎች ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ በጉዲፈቻ ፡ ልጆች ፡ መኻከል ፡ ያለው ፤ በጡት ፡ አባትና ፡ በጡት ፡ ልጅ ፤ በሞግዚትና ፡ አሳዳሪ ፤ በጌታና ፡ ባሪያ ፤ ከወገኖቹ ፡ አንዱ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለመሆን ፤ በጀንደረባነት) ፤ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፤ በበሽታ ፤ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ በማግባት ፤ አንደኛው ፡ ወገን ፡ መነኩሲት ፡ ሲሆኑ ፡ የሚስቲቱ ፡ ዕድሜ ፡ ከሰላሳ ፡ በላይ ፡ ሲሆን ፤ በባልቴትነት ፡ ጊዜ ፡ ምክንያት ፤ ፈቃድ ፡ ስላለመኖር ፤ ዕድሜ ፡ በማነስ ፡ ምክንያትና ፡ (ሴት ፡ ከ፲፪ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ወንድ ፡ ደግሞ ፡ ከሃያ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፤ የቤተክርስቲያኑ ፡ አገባብ ፡ ሳይሟላ ፡ ሲቀር ፡ ነው ።

20. እዚያው ፤ ገጽ ፡ ፻፶፯ — ፻፶፱ ።

21. የሕጉ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ውጥን ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥትን ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ እንዳለው፤ ፡ እንዲቆይ ፡ ለማድረግ ፡ ነበር ። ረነ ፡ ዳቪድ ፡ በመግለጫው ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ፡ ገጽ ፡ ፳ ፡ ይመልከቱ ።

22. በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፰፻፸፯ ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነቶች ፡ ብሔራዊ ፡ ሃይማኖታዊና ፡ በልማድ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ተብለው ፡ በሦስት ፡ መደቦች ፡ ይከፈላሉ ። የአንደኛው ፡ ወገን ፡ ሃይማኖት ፡ በመሳሳት ፡ ጋብቻው ፡ የተፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ የተሳሳተው ፡ ሰው ፡ ጋብቻውን ፡ በአንቀጽ ፡ ፰፻፲፰ ፡ መሠረት ፡ እንዲ ፈርስ ፡ ዳኞችን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

23. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፰፻፲፪ ፡ ረነ ፡ ዳቪድ ፡ በመግለጫ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ፡ ገጽ ፡ ፶፯ ፡ ይመል ከቱ ።

24. እዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፰፻፲፯ ።

25. እዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፰፻፲፱(፫) እና ፡ ፰፻፳(፫) ።

26. እዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፰፻፲፱(፩) እና (፪) ፤ ፰፻፳ (፩) እና (፪) ።

27. እዚህ ፡ ላይ ፡ voidable እና ፡ dissolution እንደ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ስንጠቀምባቸው ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ እንደየፍላጎታቸው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊያውሏቸው ፡ መቻላቸውን ፡ ማወቅ ፡ ይኖርብናል ።

ዓይነቱ ፡ መሰናክሎች ፡ አሠራር ፡ እንደየሁኔታው ፡ ይለያያል ። ይህ ፡ ክፍል ፡ ከሌሎች ፡ ክፍሎች ፡ የሚለይበት ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ጋብቻው ፡ ከሠርጉ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በኋላ ፡ ሊፈርስ ፡ የሚችልና ፡ መጨረሻውም ፡ በፍቺ ፡ የሚያልቅ ፡ ቢሆንም ፡ ከዛ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ሊጸና ፡ መቻሉን ፡ ነው ። ይህም ፡ ማለት ፡ ማን ኛውም ፡ ጋብቻ ፡ ሠርጉ ፡ ከመከናወኑ ፡ በፊት ፡ በነበረበት ፡ ጉድለት ፡ ምክንያት ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል ፡ ብለን ፡ ስናበቃ ፡ ከዛ ፡ በኋላ ፡ ባለው ፡ ጊዜም ፡ ሊጸና ፡ ይችላል ፡ የምንልበት ፡ ምክንያት ፡ መሰናክሉ ፡ የተወገደ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ጊዜው ፡ ያለፈ ፡ ሲሆን ፡ ነው ። ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ሁኔታ ፡ መጽናት ፡ ይባላል ።

ከመጀመሪያውኑ ፡ ሊፈርሱ ፡ የሚችሉ ፡ ሆነው ፡ ሊጸኑ ፡ ይችላሉ ፡ የምንላቸው ፡ ጋብቻዎች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ። አንደኛ ፡ ዕድሜያቸው ፡ በማይፈቅድላቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚደረገው ፡ ጋብቻ ።[28] ሁለተኛ ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ።[29] ሦስተኛ ፡ ራሳቸውን ፡ ባልቻሉ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚደረገው ፡ ጋብቻ ።[30] አራተኛ ፡ ኃይል ፡ በመጠቀም ፡ የሚቆመው ፡ ጋብቻ ።[31] አምስተኛና ፡ የመጨረሻው ፡ ደግሞ ፡ በሥሕተት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ጋብቻ ።[32] ሲከናወን ፡ ነው ።

የጋብቻ ፡ ቋሚነት ፡ አስተሳሰብ ፡ ከቤተ ፡ ክህነት ፡ ሕግ ፡ (Canon Law)[33] የመጣ ፡ ነው ። ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻ ፡ ጉድለት ፡ ቢገኝበትም ፡ ቅሉ ፡ ጉድለቱ ፡ ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ የተወገደ ፡ እንደሆነ ፡ ወገኖቹ ፡ ደግሞ ፡ የጋብቻ ፡ ስምምነታቸውን ፡ ካሻሻሉ ፡ ጋብቻው ፡ ቋሚ ፡ ይሆናል ። ጉድለቱ ፡ በደምብ ፡ ያልተገለጠ ፡ እንደሆነ ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ባልየውና ፡ ሚስቲቱ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ መኖር ፡ የቀጠሉ ፡ እንደሆነ ፡ ጉድለቱ ፡ በቀላሉ ፡ ሊወገድ ፡ ይችላል ። የጋብቻ ፡ ቋሚነት ፡ መፈቀድ ፡ ጋብቻው ፡ በሚገኝበት ፡ አኳኋን ፡ እንዲቀጥል ፡ በሚል ፡ ፍላጎት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሲሆን ፡ ይህ ፡ ሊሆን ፡ የሚ ችለው ፡ የባልየውና ፡ የሚስቲቱ ፡ ሁኔታ ፡ ይህንኑ ፡ ፍላጎት ፡ የሚደግፍ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ። የጋብቻ ፡ ቋሚነት ፡ በአውሮጳ ፡ አገሮችና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሲሠራበት ፡ ይታያል ።[34]

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ እንደሚለው ፡ ዕድሜያቸው ፡ በማይፈቅድላቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ጋብቻ ፡ የተከናወነ ፡ እንደሆነ ፡[35] ማንኛውም ፡ ያገባኛል ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ሕግ ፡ አስከባሪ ፡ ጋብቻው ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለማመልከት ፡ ይችላል ።[36] ዕድሜው ፡ ከተሟላ ፡ ግን ፡ ጉድለቱ ፡ ስለሚሰረዝ ፡ ከዛ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ጋብ ቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ ብሎ ፡ ማመልከቱ ፡ ከንቱ ፡ ነው ።[37] ጉድለቱ ፡ በመወገዱ ፡ ምክን ያት ፡ ጋብቻው ፡ ይጸናል ።

---

28. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፹፭ ።
29. እዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፹፮ ።
30. እዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፹፯ ፡ እና ፡ ፭፻፹፰ ።
31. እዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፹፱ ።
32. እዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፺ ።
33. ኤፍ. ጂ. ቪድ ፡ "Nullity of marriage" (ኒው ፡ የርክ ፤ ቪድ ፡ ኤንድ ፡ ዋርድ ፡ ፲፱፻፶፱) ፡ ገጽ ፡ ፴ ፡ ዲ. ላሰክ ፤ በመግለጫ ፡ ቁጥር ፡ ፲፩ ፡ የተመለከተው ። ገጽ ፡ ፩፻፶፯ ።
34. ለምሳሌ ፡ ፈረንሣይ ፤ ፖላንድና ፡ ስዊትዘርላንድ ። የማይረጋገጥና ፡ እውነትን ፡ ማውጣት ፡ አስተሳሰብ ፡ በነሞን ፡ ሎው ፡ በገሚሉ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ውጤት ፡ ነው ፡ ያለው ።
35. በአንቀጽ ፡ ፭፻፹፩ ፡ መሠረት ፡ ወንዱ ፡ እንዲያገባ ፡ የ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ልጃገረዷ ፡ ደግሞ ፡ የ፲፭ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ሊኖራቸው ፡ ይገባል ።
36. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ፮፻፶፰(፩) ።
37. እዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፶፮(፪) ።

እንደዚሁም ፡ አንድ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ራሱን ፡ የማይችል ፡ ሰው ፡ ለጋብቻ ፡ የተመደበለት ፡ ፈቃድ ፡ ሳያገኝ ፡ ካገባ ፡[38] እና ፡ ደግሞ ፡ እንዳያገባ ፡ የሚከለክለው ፡ የችሎታ ማነስ ፡ ምክንያት ፡ የተወገደ ፡ እንደሆነ ፡ ሰውዬው ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ ማመልከት ፡ የሚችልበት ፡ ጊዜ ፡ ራሱን ፡ ከቻለበት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ብቻ ፡ ነው ።[39] ጋብቻ ፡ መፍቀድ ፡ ይገባው ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡[40] ጋብቻው ፡ መከናወኑ ፡ ካወቀበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ጋብቻውን ፡ ለማፍረስ ፡ ማመልከቻውን ፡ ሊያቀርብ ፡ ቢችልም ፡ የችሎታው ፡ ማነሱ ፡ ምክንያት ፡ የተወገደ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ።[41]

በኃይል ፡[42] ወይም ፡ በስሕተት ፡[43] የተመሠረተ ፡ ጋብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ የማመልከት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ የተበደለው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ። ተበዳዩ ፡ ማመልከቻውን ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ በኃይል ፡ መጠቀሙ ፡ ካቆመበት ፡[44] ወይም ፡ ደግሞ ፡ ስሕተቱ ፡ ከታወቀበት ፡[45] ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ጋብቻው ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ባለው ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ጊዜው ፡ መወሰኑ ፡ የሚያሳየው ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ እንቅፋት ፡ (መሰናክል) ፡ ቢኖር ፡ የጋብቻው ፡ መቆየትን ፡ ሲሆን ፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ ጋብቻው ፡ ዘላቂነት ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ ሐሳብ ፡ ማቅረቡ ፡ ጉድለቱ ፡ እስካሁን ፡ ተወግዶአል ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ወገኖቹ ፡ ተስማምተዋል ፡ በሚል ፡ እምነት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ።

---

38. በአንቀጽ ፡ ፫፻፲ ፡ እንደተመለከተው ፡ ማንኛውም ፡ ዕድሜው ፡ ለጋብቻ ፡ ከተመደበው ፡ ወሰን ፡ በታች ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ እንዲያገባ ፡ የሞግዚቱ ፡ ፈቃድ ፡ ማግኘት ፡ ይኖርበታል ። ይህ ፡ አኳኋን ፡ ሊሠራበት ፡ የሚችለው ፡ በልጃገረዶች ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የምንልበት ፡ ምክንያት ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ከ፲፰ ፡ በታች ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ለማግባት ፡ ስለማይችል ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፹፪(፪) ፡ የሚያሳየውን ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ መኖሩን ፡ በማስታወስም ፡ ጭምር ፡ ነው ። በአንቀጽ ፡ ፫፻፳፱ (፩) መሠረት ፡ በፍርድ ፡ የተከለከለ ፡ ሰው ፡ ዳኞች ፡ ካልፈቀዱለት ፡ በቀር ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ መዋዋል ፡ አይችልም ።

39. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፹፩(፩) ፡ እና ፡ (፪) ።

40. እዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፹፩(፩) ፡ እና ፡ (፫) ።

41. እዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፹፩(፩) እና ፡ (፫) ፡ በአንቀጽ ፡ ፭፻፹፮ ፡ እና ፡ ፫፻፳፱(፫) ውስጥ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ልዩነት ፡ ያለው ፡ በፍርድ ፡ የተከለከለ ፡ ሰው ፡ ጋብቻ ፡ በሚፈርስበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። በአንቀጽ ፡ ፫፻፳፱(፫) እንደተመለከተው ፡ ማንኛውም ፡ ያገባ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ጋብቻውን ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ። አንቀጽ ፡ ፭፻፹፮ ፡ ከሌሎች ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ የሚያወሱ ፡ አንቀጾች ፡ ስለሚስማማ ፡ ለትክክለኛነቱ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ።

42. በኃይል ፡ መጠቀም ፡ ፈቃደኝነትን ፡ የሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ ያበላሻል ። ይህም ፡ የሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ተበዳዩ ፡ ወገን ፡ ራሱን ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ የቅርብ ፡ ቤተሰቦቹን ፡ በአንቀጽ ፡ ፭፻፹፫(፩) እና ፡ (፪) መሠረት ፡ ለማዳን ፡ ፈቃድ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። የዚህኑ ፡ ዓይነት ፡ ምሳሌ ፡ ለማግኘት ፡ በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ፔትሮን ፡ ማቲልዴ ፡ ስርፓጊ ፡ (ኩር ፡ ደ ፡ አፔል ፡ ደ ፡ ባስቲያ ፡ ፍሬ ፡ ጁን ፡ ፳፯ ፡ ፲፱፻፶፱) ፡ ዳሎዝ ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ በገጽ ፡ ፬፻፲፯ ፡ ይመልከቱ ።

43. መሳሳት ፡ ፈቃደኝነትን ፡ የሚያጠፋው ፡ ዋና ፡ መሳሳት ፡ ሲሆን ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ማለት ፡ በሚያገቡት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ መሳሳት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። አንቀጽ ፡ ፭፻፹፬ ፡ ዋና ፡ ስህተቶች ፡ የሚባሉት ፤ በሰውየው ፡ መልክ ፤ በሃይማኖቱ ፤ በጤናውና ፡ በችሎታው ፡ ምክንያት ፡ የሚመጡ ፡ መሆናቸውን ፡ ይገልጻል ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ይመደባል ፡ ወይም ፡ አይመደብም ፡ ብሎ ፡ ለመናገር ፡ የሚያስችል ፡ አባባል ፡ ነው ፡ ያለው ፡ የፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ተመሳሳይ ፡ ቢሆንም ፡ የሰውየውን ፡ አገር ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ የሰየውን ፡ ጠባይ ፡ በመሳሳት ፤ ጀንደረባነቱን ፡ ባለማወቅና ፡ የሰውየውን ፡ መልክ ፡ በመሳሳት ፡ የሚሆን ፡ ነው ፡ ይላል ። በ ፡ ፒ. ኤስሜይን ፡ የተሰጠውን ፡ መግለጫ ፡ እዩ ፡ ዳሎዝ ፡ ፩ሺ.፱፻፶፱ ፡ ገጽ ፡ ፱፻፶፯ ።

44. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፹፬(፩) እና ፡ (፪) ።

45. እዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፹፭(፩) ፡ እና ፡ (፪) ።

በጋብቻ ፡ ላይ ፡ የሚፈጸመው ፡ ጋብቻ ፡[46] በተጋቢዎቹ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በሕግ ፡ አስከባሪው ፡[47] አመካኝነት ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል ። የዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻ ፡ ሊጸና ፡ የሚችለው ፡ በመጀመሪያው ፡ ጋብቻ ፡ ቀድሬ ፡ የነበረችው ፡ ሚስት ፡ ስትሞት ፡ ነው ።[48]

ሊፈርሱ ፡ የሚችሉ ፡ ሆነው ፡ ቋሚ ፡ ሊሆኑም ፡ ይችላሉ ፡ የምንላቸውን ፡ ጋብቻ ዎች ፡ መሰናክል ፡ ያለባቸው ፡ መሆኑን ፡ እያወቁ ፡ የሠርጉን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቢያከብሩ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ተካፋይ ፡ ቢሆኑ ፡ በወንጀል ፡ ይቀጣሉ ።[49] በወንጀል ፡ መቀጣቱ ፡ ቢኖርም ፡ ቅሉ ፡ ጋብቻው ፡ እንዳለው ፡ እንዲቀጥልና ፡ ቋሚም ፡ እንዲሆን ፡ የሚለው ፡ ሐሳብ ፡ የሚሰነዘረው ፡ ጉድለቱ ፡ ስለሚጠፋ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የጉድለቱ ፡ ጠቃሚነት ፡ ሳያስፈልግ ፡ ሲቀርም ፡ ጭምር ፡ ነው ።

ሦስተኛውና ፡ የመጨረሻው ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ ፍጹም ፡ መሰናክል ፡ የሚባለው ፡ ነው ። በዚሁ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የተመደቡት ፡ መሰናክሎች ፡ ጥልቅ ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሳ ፡ ሊስተካከሉ ፡ ወይም ፡ ሊጠገኑ ፡ አይችሉም ፤ ስለዚህ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ጋብቻው ፡ ቋሚ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ፍጹም ፡ መሰናክል ፡ የሚለው ፡ ስነ ፡ ሐሳብ ፡ የምንጠቀምበት ፡ በሥጋና ፡ በጋብቻ ፡ የሚዛመዱት ፡ ሰዎች ፡ እንዳይጋቡ ፡ የሚከለከላ ቸው ፡ ሲሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ።[50] ይህ ፡ የተባለው ፡ መሰናክል ፡ ቢከለከላቸውም ፡ በግድ የለሽነት ፡ የተጋቡ ፡ እንደሆነ ፡ ጋብቻው ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል ። ጋብቻው ፡ ሊፈርስ ፡ የሚችለው ፡ በማንኛውም ፡ ያገባኛል ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ጠያቂነት ፡ ብቻ ፡ ነው ።[51] መሰናክሉ ፡ በፍጹም ፡ ሊወገድ ፡ ስለማይቻል ፡[52] ጋብቻው ፡ ምንጊዜም ፡ ቋሚ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ጋብቻው ፡ በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ መሰናክል ፡ መኖሩን ፡ እያወቁ ፡ ወይንም ፡ ደግሞ ፡ ማወቅ ፡ ሲገባቸው ፡ ጋብ ቻው ፡ እንዲፈጸም ፡ የረዱ ፡ ሰዎች ፡ በወንጀል ፡ ይቀጣሉ ።[53]

46. በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ ማግባትን ፡ እንደሚጨምር ፡ የሚያጠራጥር ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ የዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ በአንቀጽ ፡ ፮፻፲፱ ፡ እና ፡ ፮፻፲፫ ፡ መሠረት ፡ የሰም ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ ይቻላል ።

47. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፲፮ (፩) ።

48. እዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፲፫ ።

49. እዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፷ ፡ ፮፻፲፭ ፤ ፮፻፲፬ ፡ እና ፡ ፮፻፲፮ ። የግል ፡ ጉዳይ ፡ በመሆኑ ፡ ስህተቱ ፡ ይታለፋል። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የተጠቀሱት ፡ የወንጀለኛ ፡ ቅጣቶች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፲፬ ፡ እና ፡ ፮፻፲፭ ፡ የተጻፉት ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ለሚቀበቅባቸው ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ አሟልቶ ፡ አይተነትንም ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ እንደየሁኔታው ፡ በወንጀል ፡ ያስቀጣል ፡ ብሎ ፡ ሲያበቃ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ ስለዚሁ ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ አይልም ። ለተባለው ፡ ተገቢ ፡ ቅጣት ፡ መወሰን ፡ ወገኖቹ ፡ ጋብቻውን ፡ ለማፍረስ ፡ እንዳያመለክቱ ፡ ስለሚገታቸው ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ።

50. እዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፹፪ ፡ ፭፻፹፫ ፡ እና ፡ ፭፻፹፬ ፡ ሦስቱን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ግልባጮች ፡ አወዳድር ፤ የእንግሊዝኛው ፡ የአማርኛው ፡ ግልባጮች ፡ የሥጋ ፡ ዘመዶች ፡ ሊጋቡ ፡ የሚችሉት ፡ ከ፯ ፡ ትውልድ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ የፈረንሣይኛው ፡ ግን ፡ በደረጃ ፡ (degree) ብሎ ፡ ጭጭ ፡ ይላል ። የጋብቻ ፡ ዘመዶች ፡ ገደብ ፡ እስከ ፡ ሦስተኛ ፡ ደረጃ ፡ ይሆናል ።

51. እዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፬ ።

52. የመጀመሪያው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ንድፍ ፡ ዝምድናውን ፡ ያስገኘው ፡ ጋብቻ ፡ ሲፈርስ ፡ ዝም ድናውም ፡ አብሮ ፡ ይቀራል ፡ ይላል ። ወደ ፡ ፓርላማ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ ንድፉ ፡ ተሻሽሎ ፡ የዚሁ ፡ ነገር ፡ በአንቀጽ ፡ ፭፻፶፭ ፡ እናገኘዋለን ። አር ፡ ዳቪድ ፡ በመግልጫ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ፡ ገጽ ፡ ፶፫ ፡ ይመልከቱ ። ኤር ፡ ኤን ፡ ፩ ፡ እና ፡ ፯ ፡ ቀቁኖኛች ፡ ትቁንቲ ፡ ሮር ፡ ፕሮብሌምስ ፡ ኢን ፡ ፋሚሊ ፡ ሎው ፡ (፲፱፻፷፫ ፡ ያልታተመ ፤ የሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ) ፡ ፕሮብሌም ፡ ፱ ፡ እና ፡ "ፈተናዎች ፡" የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ፫ ፡ (፲፱፻፷፪) ።

53. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፲ ።

በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ማንኛውም ፡ ጋብቻ ፡ እንደየሁኔታው ፡ የሚለያይ ፡ መሰናክል ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ፍጹም ፡ መሰናክል ፡ ሲኖርበት ፡ ሊፈርሱ ፡ ይችላሉ ፡ ከምን ላቸው ፡ መደቦች ፡ አንዱ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። የመጀመሪያው ፡ ቋሚ ፡ እስኪሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል ፡ ስንል ፤ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሊፈርስ ፡ ይች ላል ፡ እንለዋለን ። በነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ ተመድቦ ፡ የምናገኘው ፡ ጋብቻ ፡ በሚፈር ስበት ፡ ጊዜ ፡ ድሮ ፡ ያስከተላቸውን ፡ ነገሮች ፡ እንደያዘ ፡ ይቀራል ። ጋብቻው ፡ ከመጀ መሪያውኑ ፡ ፈራሽ ፡ ወይም ፡ ውድቅ ፡ የሚሆነው ፡ ግን ፡ exnunc ሲሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ባለ ፡ መጽናቱ ፡ ምክንያት ፡ የፈረሰ ፡ ጋብቻ ፡ ውጤት ፡ በፍች ፡ ከፈረሰ ፡ ጋብቻ ፡ ውጤት ፡ ተመሳሳይ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። የጋብቻ ፡ ማፍረስ ፡ ለመጪው ፡ ጊዜ ፡ ውጤት ፡ እንዳይ ኖረው ፡ ሊከለክል ፡ ኃላፊነት ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲሆን ፡ ጋብቻውን ፡ ማፍ ረስ ፡ ያለበት ፡ ፍትሕን ፡ በመመርኰዝ ፤ በፍች ፡ ሕጎች ፡ በመመራት ፤ የወገኖችን ፡ (ተጋቢዎቹ) ፡ መጥፎ ፡ ወይም ፡ ቅን ፡ ልቦናን ፡ በመመርመር ፤ ሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ መፈጸሙ ንና ፡ አለመፈጸሙን ፡ በማረጋገጥና ፡ እንዲሁም ፡ ከጋብቻው ፡ የተወለዱትን ፡ ልጆችና ፡ በቅን ፡ ልቦና ፡ የተጠና ፡ የሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ጥቅምን ፡ በማመዛዘን ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ ይኖርበታል ።[54] ሊፈርስ ፡ የሚችል ፡ ጋብቻ ፡ እስኪፈርስ ፡ ድረስ ፡ እንደቋሚ ፡ ጋብቻ ፡ ስለሚቆጠርና ፡ የሚያስከትለውም ፡ ውጤት ፡ ፍች ፡ ከሚያስከትለው ፡ ስለሚመሳሰል ፡ የጋብቻው ፡ መፍረስ ፡ ለወደፊቱ ፡ ይመጣ ፡ ይሆናል ፡ በሚል ፡ አስተሳሰብ ፡ ላይ ፡ የተ መሠረተ ፡ ነው ። የጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ መፈጸም ፡ ወይም ፡ የቅርብ ፡ ሥጋ ፡ ዝምድና ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ በሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ መገናኘት ፡ ጋብቻ ፡ ወይም ፡ ግንኙነቱ ፡ ቢፈ ርስም ፡ ድሮ ፡ የነበረውን ፡ የቋሚነት ፡ ግምት ፡ እንደያዘ ፡ ይቀራል ።

አንድ ፡ ጋብቻ ፡ ሊፈርስ ፡ የሚችል ፡ ሆኖ ፡ ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ የፈረሰ ፡ እንደሆነ ፡ ዱሮውም ፡ ፈራሽ ፡ ነበር ፡ የሚለውን ፡ አስተሳሰብ ፡ አሚልቶ ፡ የሚገልጽ ፡ ምሳሌ ፡ አልተገኘም ። ስለዚህ ፡ ስለቀድሞው ፡ ሁኔታ ፡ የሚሰነዘሩትን ፡ ጥያቄዎች ፡ ስለሚያ ስወግድ ፡ ፖሊሲው ፡ ቀላልና ፡ ተገቢ ፡ ይመስላል ።

## III

### የጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ሁናቴ ።

ቀደም ፡ ብለን ፡ እንደገለጥነው ፡ ጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ሊፈርስ ፡ የሚችሉ ፡ ሆነው፡ ደግሞም ፡ ቋሚ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ፡ ከምንላቸው ፡ የጋብቻ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ የሚመደበው ። የጋብቻው ፡ መፍረስ ፡ እስኪወግደው ፡ ድረስ ፡ በጋብቻው ፡ ላይ ፡ የተ ያያዘው ፡ የቀዋሚነት ፡ ግምት ፡ እንዳለ ፡ ይቀጥላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ከሌሎቹ ፡ ጋብቻዎች ፡ የሚለይበት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ። ይኸውም ፡ ቋሚነቱ ፡ የሚታወቀው ፡ የመጀመሪያዬቱ ፡ ሚስት ፡ በምትሞትበት ፡ ጊዜ ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ እንደሌሎቹ ፡ ጋብቻዎች ፡ በቀጥታ ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ አለመምጣቱን ፡ ነው ። ከዚህ ፡ የተነሳም ፡ አንዳንድ ፡ ችግሮች ፡ ያጋጥሙናል ።

የሚያስከትሉትም ፡ ጥያቄ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ፡— በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በጋብቻ ፡ ላዩ ፡ ጋብቻ ፡ ምን ፡ ሥፍራ ፡ አለው? በመሠረቱ ፡ ሕጋዊ ፡ ሆኖ ፡ መገመት ፡ አለበት ፡ በሚባለው ፡ ሃሳብ ፡ ሊገለገል ፡ ይችላል ፡ ወይ?

---

54. እዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፺፯ (፩) እና ፡ (፫) ። በስዊስ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ውጤቶች ፡ የፍችውም ፡ ናቸው ፤ የስዊስ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፻፶፬ም ፡ እንደዚሁ ፡ ይላል ።

ቁጥር ፣ ፭፻፹፭ ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፡— "አንድ ፣ ሰው ፣ አስቀድሞ ፣ በጋብቻ ፣ የተሳሰረ ፣ ከሆነ ፣ ጋብቻው ፣ እስከቆየ ፣ ድረስ ፣ ሁለተኛ ፣ ጋብቻ ፣ ለማድረግ ፣ አይችልም ።" ቢሆንም ፣ አንዳንድ ፣ ቀደም ፣ ብለው ፣ ያገቡት ፣ ሰዎች ፣ የትዳር ፣ ጓደኛ ፣ እያላቸው ፣ የጋብቻ ፣ ሥርዓት ፣ ይፈጽማሉ ። ይህ ፣ ከተደረገ ፣ "ሕግ ፣ በሚያጸናው ፣ ዐይነት ፣ በጋብቻ ፣ ሥርዓት ፣ ግዴታ ፣ ታስሮ ፣ በሚገኝበት ፣ ጊዜ ፣ የፊተኛው ፣ የጋብቻ ፣ ሥርዓት ፣ ሳይፈርስ ፣ ከሌላ ፣ ሴት ፣ ጋር ፣ የጋብቻ ፣ ሥርዓት ፣ መፈጸም ፡"[55] በወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ ወንጀል ፣ ነው ። በጋብቻ ፣ ላይ ፣ ጋብቻ ፣ ያደረጉት ፣ ሁለቱ ፣ ተጋቢዎች ፣ ቅጣት ፣ ሊሰነዘርባቸው ፣ ይችላል ። ከዚህኛው ፣ ለየት ፣ ያለው ፣ "በጋብቻ ፣ ላይ ፣ ጋብቻ ፣ ያደረገው ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ እንደሚፈቅደው ፣ አኗኗር ፣ ወይም ፣ ልማድ ፣ እንደሆነ ፣ ከዚህ ፣ በላይ ፣ በተጻፈው ፣ ቁጥር ፣ የተወሰነው ፣ ድንጋጌ ፣ አይፈጸምበትም ፡"[56] የሚለው ፣ የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ውስጥ ፣ የሚገኘው ፣ ቁጥር ፣ ነው ። እንደዚህ ፣ ያለ ፣ ልዩነት ፣ የሚፈጥር ፣ ቁጥር ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ውስጥ ፣ ስለሌለ ፣ ቁጥር ፣ ፭፻፹፭ ፣ የበላይነት ፣ ይኖረዋል ። የእስላም ፣ ሃይማኖት ፣ ያላቸው ፣ ሰዎች ፣ ይህን ፣ የመሰለ ፣ ለየት ፣ ያለ ፣ ሕግ ፣ በአንቀጽ ፣ ፳፬ ፣ ውስጥ ፣ እንዲደነገግላቸው ፣ የፍትሐ ፣ ብሔሩን ፣ ሕግ ፣ ያረቀቁት ፣ ሰው ፣ ፍላጎት ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ተርጓሚዎቹ ፣ ሥራ ፣ ስለበዛባቸው ፣ የመጀመሪያው ፣ ንድፍ ፣ ሳይተረጐም ፣ ክርክርም ፣ ሳይደረግበትና ፣ ለፓርላማውም ፣ ሳይቀርብ ፣ ቀረ ።[57] ስለዚህ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ሕግ ፣ የሚያውቀው ፣ አንድ ፣ ባል ፣ ካንድ ፣ ሚስት ፣ አንድ ፣ ሚስት ፣ ካንድ ፣ ባል ፣ ጋር ፣ የተደረገውን ፣ ጋብቻ ፣ ብቻ ፣ ነው ።[58]

ባልና ፣ ሚስት ፣ በጋብቻ ፣ ላይ ፣ ጋብቻ ፣ ያከናወኑ ፣ እንደሆን ፣ ከተጋቢዎቹ ፣ አንዱ ፣ ወይም ፣ ዐቃቢ ፣ ሕጉ ፣ ጋብቻው ፣ እንዲፈርስለት ፣ ሊያመለክት ፣ ይችላል ።[59]

ሁለተኛ ፣ ጋብቻ ፣ በተከበረበት ፣ ዕለት ፣ የመጀመሪያው ፣ ባል ፣ ወይም ፣ ሚስት ፣ በሕይወት ፣ መኖሩን ፣ ወይም ፣ አለመኖሩን ፣ ማረጋገጥ ፣ የቢላሹ ፣ ፋንታ ፣ ነው ።[60] እዚህ ፣ ላይ ፣ የፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ሕግ ፣ ግልጽ ፣ አይደለም ። መጀመሪያ ፣ ነገር ፣ ጋብቻው ፣ እንዲፈርስ ፣ የሚያስፈልገው ፣ ማረጋገጫ ፣ የመጀመሪያው ፣ ሚስት ፣ ወይም ፣ ባል ፣ ጋብቻው ፣ እንዲፈርስ ፣ በተጠየቀበት ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ በጋብቻ ፣ ላይ ፣ ጋብቻ ፣ በተፈጸመበት ፣ ጊዜ ፣ አይደለም ። በዚህ ፣ ምክንያት ፣ ቁ. ፭፻፲፫ ፣ "በጋብቻ ፣ ላይ ፣ ጋብቻ ፣

55. ወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ቁ. ፮፻፲፮ ።

56. ወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ቁ. ፮፻፲፮ ።

57. ሬኔ ፣ ዳቪድ ፣ በገጽ ፣ ፺ ፣ በ፲፯ኛው ፣ መግለጫ ፣ ላይ ፣ እንዳመለከቱት ፣ ሕግ ፣ ይሆናል ፣ ተብሎ ፣ ሃሳብ ፣ የቀረበው ፣ ቁጥር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፡— "ቁ. ፫ሺ፫፻፵፯ ፣ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ (፩) ባልየው ፣ እስላም ፣ ከሆነ ፣ ጋብቻው ፣ ሊፈርስ ፣ የሚችለው ፣ በዐቃቤ ፣ ሕጉ ፣ ጥያቄ ፣ ብቻ ፣ ነው ።"
(፪) የፍርድ ፣ ሚኒስትሩ ፣ ልዩ ፣ ጥያቄ ፣ ካላቀረቡ ፣ በሰተቀር ፣ በሕግ ፣ የተደነገገው ፣ ጊዜ ፣ እስኪደርስ ፣ ድረስ ፣ ዐቃቤ ፣ ሕጉ ፣ ጥያቄ ፣ ሊያቀርብ ፣ አይችልም ።"

58. ነገር ፣ ግን ፣ እስላሞች ፣ ግላዊ ፣ የሆኑትን ፣ ተግባራቸውን ፣ የሚያስተዳድሩት ፣ በነጋሪት ፣ ጋዜጣ ፣ ቁ. ፱ ፣ ሦስተኛ ፣ ዓመት ፣ በ፲፱፻፴፮ ፣ ዓ. ም. በወጣው ፣ የቃዲና ፣ የሸሪያ ፣ ፍ/ቤቶች ፣ አዋጅ ፣ መሠረት ፣ ስለሆነ ፣ ባንድ ፣ ሚስት ፣ ወይም ፣ ባንድ ፣ ባል ፣ አይወሰኑም ። የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ቁ. ፫ሺ፫፻፵፯ ፣ የእስላምን ፣ ሕግ ፣ ሽሮት ፣ ይሆናል ፣ የሚባለውም ፣ ሃሳብ ፣ ትክክለኛ ፣ ቢሆንም ፣ የላይኛው ፣ ሃሳብ ፣ ይረጋል ።

59. የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ቁ. ፭፻፹፰(፩) ፣ በጋብቻ ፣ ላይ ፣ ጋብቻ ፣ የፈጸመው ፣ ተጋቢ ፣ (ባል ፣ ወይም ፣ ሚስት ፣) በጋብቻ ፣ ላይ ፣ ጋብቻው ፣ እንዲፈርስለት ፣ የመጠየቅ ፣ መብት ፣ የለውም ። እራሱ ፣ በወንጀለኛ ፣ ሕግ ፣ ሊቀጣ ፣ መቻሉን ፣ ተገንዝቦ ፣ ጉዳዩን ፣ ለዐቃቤ ፣ ሕጉ ፣ ሊያቀርብ ፣ ይችላል ።

60. የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ቁ. ፭፻፹፰(፪) ።

የሚጸናው ፡ የመጀመሪያው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ሲሞት ፡ ነው ።” በዚህ ፡ አስተ ሳሰብ ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ በተደረገበት ፡ ዕለት ፡ የመጀመሪያው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ በሕይወታቸው ፡ እያሉ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈረስ ፡ በተጠየቀበት ፡ ጊዜ ፡ ሊሞቱ ፡ ይችላሉ ። ጋብቻው ፡ በነዚህ ፡ በሁለቱ ፡ ጊዜያት ፡ መካከል ፡ ሕጋዊ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ ሁለተኛው ፡ ጋብቻ ፡ ሊፈርስ ፡ የሚችለው ፡ በፍቺ ፡ ነው። ሁለተኛ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ቁ. ፲፱፻፫ ፡ ግልጽ ፡ ቢሆን ፡ አንድ ፡ ሌላ፡ጥያቄ ፡ ያስከትላል ። የመጀመሪያው ፡ ጋብቻ ፡ ቁ. ፲፱፻፫ ፡ እንደሚያመለክተው ፡ በሞት ፡ ሳይሆን ፡ በፍቺ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ሁኔታዎች ፡ ባለመጠበቃቸው ፡ የተነሣ ፡ በሚሰነዘረው ፡ ቅጣት ፡ የፈረሰ ፡ እንደሆን ፡ ምን ፡ ይደረጋል? በጋብቻ ፡ ላይ ፡ የሚደረገውን ፡ ጋብቻ ፡ ሕጋዊ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል? ጋብቻውን ፡ የሚያሰናክል ፡ ነገር ፡ ስለሌለ ፡ ለዚህ ፡ የያቄ ፡ ቀጥተኛ ፡ መልሱ ፡“አዎን ፡” ማለት ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ከኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ተመሳ ሳይ ፡ የሆነው ፡ የፖላንድ ፡ ሕግ ፡ የቀድሞው ፡ ጋብቻ ፡ ያበቃበትን ፡ ምክንያት ፡ ሳይሻ ፡ ጋብቻው ፡ ሕጋዊ ፡ እንዲሆን ፡ ይፈቅዳል ።[61] የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የፖላንዱን ፡ ሕግ ፡ ምሳሌ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ የሚከተል ፡ አይመስልም ። ይህም ፡ የሆነበት ፡ በፖላንዱ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ በተሰነዘረው ፡ ትችት ፡ ምክንያት ፡ ነው ። የፖላንድ ፡ ተችዎች ፡ በፍቺ ፡ ምክንያት ፡ የፈረሰውን ፡ የቀድሞ ፡ ጋብቻ ፡ ሕጋዊ ፡ ማድረጉ ፡ በተለይ ፡ አስጸያፊ ፡ አድራጎት ፡ አድርገው ፡ ይቆጥሩታል ። ባልና ፡ ሚስት ፡ እንዲፋቱ ፡ ሊገፉፉ ፡ ይችላል ፡ በማለት ፡ ነው ።[62]

ውጤት ፡ የሌላቸውን ፡ ጋብቻዎች ፡ በጠቅላላው ፡ ስንመለከት ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻን ፡ ሕጋዊ ፡ ማድረጉ ፡ ከነዚህ ፡ ጋር ፡ ይስማማል ። እንዲህም ፡ ሆኖ ፡ ሕጉ ፡ ለውጥ፡ ፈላጊ ፡ (ሪቮሉሽነሪ) ፡ ነው ።

በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ማድረግ ፡ ወንጀል ፡ ነው ። በብዙ ፡ አገሮችም ፡ ምንም ፡ ዓይ ነት ፡ ውጤት ፡ ለማስከተል ፡ የማይችል ፡ ድርጊት ፡ ነው ። በስዊትዘርላንድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ሊጸድቅ ፡ የሚችለው ፡ ይህንን ፡ ድርጊት ፡ አከናዋኙ ፡ በቅን ፡ ልቡናው ፡ ያደረገ ፡ እንደሆን ፡ ነው ።[63] በፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ምንም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ሕጋዊ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።[64] የፖላንድም ፡ ሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ጋብቻን ፡ ከማጽደቃቸው ፡ በፊት ፡ የሰውየውን ፡ ቅን ፡ ልቦና ፡ አይመለከቱም ።

የጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ሁኔታ ፡ የተረጋገጠ ፡ ባለመሆኑ ፡ በግላዊ ፡ አቋም ፡ ላይ ፡ ችግር ፡ አስከትሏል ። በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ ሁለተኛ ፡ ሚስቱ ፡ ብትለ

---

61. የፖላንድ ፡ የቤተሰብና ፡ የአሳዳሪ ፡ ሕግ ፡ (ተርጓሚው ፡ ጂ ፡ ጐራኪ ፤ ከዲ ፡ ላሶክ ፡ የፖላንድ ፡ የቤተሰብ ፡ ሕግ ፡ ሌይደን ፤ ኤ ፡ ዳብሊው ፡ ሲጆቶፍ ፡ ፩ሺ፱፻፷፰ ዓ. ም.) ፤ ገጽ ፡ ፪፻፴፮ ፤ ቁ. ፲፫ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — “ክፍል ፡ ፫ ፡ —የቀድሞው ፡ ጋብቻ ፡ ካበቃ ፡ ወይም ፡ ከፈረሰ ፡ ከተጋቢዎቹ ፡ አንዱ ፡ በመካሄድ ፡ ላይ ፡ በሚገ ኘው ፡ ጋብቻ ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ጋብቻው ፡ ሊፈርስ ፡ አይችልም ።”

62. ዲ ፡ ላሶክ ፤ ከላይ ፡ በግርጌ ፡ መግለጫ ፡ ቁ. ፰፮ ፤ ገጽ ፡ ፪፻፳፪ ፡ ተመልከቷል ።

63. የእስዊስ ፡ ፍ/ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቁ. ፻፳፱ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ። “የመጀመሪያው ፡ ጋብቻ ፡ ፈርሶ ፡ እንደሆነና ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ያከናወነው ፡ ወገን ፡ ባለቤት ፡ በቅን ፡ ልቡናው ፡ ካደረገ ፡ ጋብቻው ፡ እንዳልነ በረ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም” ።

64. የመጀመሪያው ፡ ጋብቻ ፡ ከፈረሰ ፡ በኋላ ፡ ጋብቻው ፡ እንዳልነበረ ፡ እንዲሆን ፡ ማመልከቻ ፡ ማቅረብ ፤ ይቻላል ። ይህ ፡ ጉድለት ፡ ካለባቸው ፡ ጋብቻዎች ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ አይደለም ፤ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ማድረግ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ በመሆኑ ፡ ይህንን ፡ ድርጊት ፡ ማጽደቁ ፡ አይቻልም ። ኤም ፡ ፕላኒዮል ፡ እና ፡ ጂ ፡ ሪፐርት ፤ ትሬቴ ፡ ፕራቲክ ፡ ዱ ፡ ድሩዋ ፡ ሲቪል ፡ (ሁለተኛ ፡ መጽሐፍ ፤ ፲፱፻፶፬ ፡ በሯሰት ፡ አበጋጅነት ፡ ሊብሬር ፡ ጀኔራል ፡ ዱ ፡ ዱ ፡ ድሩዋ ፡ ጅሩስፕሩደንስ) ፡ ቮልዩም ፡ ፪ ፡ ቁ. ፪፻፳፯ ።

የውና ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ቢያገባት ፡ ሁለተኛውም ፡ ጋብቻ ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ሆኖ ፡ ሊቆጠር ፡ ይችላል ፡ ወይ? ተመሳሳይ ፡ ሕግ ፡ ያላቸው ፡ አገሮች ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻን ፡ ለመደገፍ ፡ ሲባል ፡ የመጀመሪያውን ፡ ጋብቻ ፡ ሕግ ፡ ወጥ ፡ አድርገው ፡ ይቆጥሩታል ።[65] በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ የፈጸመው ፡ ሰው ፡ ጋብቻው ፡ በመካሄድ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ቢሞት ፡ በጋብቻው ፡ ላይ ፡ ተቃውሞ ፡ ወይስ ፡ በሕይወት ፡ ያሉትን ፡ ሁለት ፡ ሚስቶች ፡ ሕግ ፡ ያውቃቸዋል? እዚህ ፡ ላይ ፡ ሁለተኛ ፡ ጋብቻ ፡ ያፈራቸው ፡ ልጆች ፡ አቋም ፡ ችግር ፡ የማያስከትልበት ፡ ምክንያት ፡ ልጆቹ ፡ ከማን ፡ እንደተወለዱ ፡ በቀላሉ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ስለሚችሉ ፡ ነው ።[66]

የፍ/ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ መጀመሪያ ፡ ንድፍ ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ አንድ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ አቋም ፡ ሰጥቶታል ። ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ እንደማድረግ ፡ ይቆጠር ፡ ነበር ።[67] እንደዚህ ፡ የሚለው ፡ ቁጥር ፡ በፍ/ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ቢገኝ ፡ ኖሮ ፡ ስለሁለተኛው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ መብት ፡ ማወቅ ፡ አያዳግትም ፡ ነበር ። እንዳጋጣሚ ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ ስላልተደረገ ፡ ለጥያቄው ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ መልስ ፡ አልተገኘለትም ።

በቅርቡ ፡ ይህንኑ ፡ ችግር ፡ ያዘለ ፡ አንድ ፡ ክስ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ነበር ።[68] የነገሩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ፦ የሟቹ ፡ ሚስቶች ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ ሁለት ፡ ሴቶች ፡ አውራጃ ፡ ፍ/ቤት ፡ ቀረቡ ። ከሳሿ ፡ ሁለት ፡ መዝገቦች ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረበች ። አንደኛው ፡ ጋብቻው ፡ በ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ. ም. መከበሩን ፡ የሚያመለክት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ነበር ። ተከሳሿም ፡ የሟቹ ፡ ሚስት ፡ መሆንዋንና ፡ አምስቱ ፡ ልጆችዋም ፡ የሟቹ ፡ ወራሾች ፡ መሆናቸውን ፡ አመለከተች ። ጉዳዩ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍ/ቤት ፡[69] ቀርቦ ፡ ፍ/ቤቱም ፡ በጋብቻው ፡ መዝገብና ፡ በምስክሮቹ ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ ከሳሿ ፡ የሟቹ ፡ የሕግ ፡ ሚስት ፡ ናት ፡ ብሎ ፡ ፈረደ ። ከሳሿ ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ጋና ፡ ለመሄድ ፡ የሚያስችላትን ፡ የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ እንዲሰጣት ፡ ለውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስታመለክት ፡ ፈት ፡ መሆንዋን ፡ ገልጣ ፡ ነበር ፡ የሚለውን ፡ ማስረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አልተቀበለውም ። ከሳሿ ፡ ጋና ፡ በነበረችበት ፡ ጊዜ ፡ አግብታ ፡ ነበር ፤

65. በፈረንሳይ ፡ ሕግ ፤ በፍ/ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፻፹፱ ፡ መሠረት ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻን ፡ ያከናወነው ፡ ወገን ፡ የመጀመሪያው ፡ ጋብቻ ፡ እንዳልነበር ፡ ይቆጠር ፡ ብሎ ፡ መከላከያ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ። ቁጥሩም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦— "አዲስ ፡ ተጋቢዎቹ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ጋብቻ ፡ ሕጋዊነት ፡ ከተቃወሙ ፡ የዚሁ ፡ ጋብቻ ፡ ሕጋዊነት ፡ ወይም ፡ ፈራሽነት ፡ በቅድሚያ ፡ መወሰን ፡ አለበት ።" የኢጣልያ ፡ ፍ/ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፻፳፬ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ።

66. በፍ/ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፯፻፷ ፡ መሠረት ፡ ልጆቹ ፡ ከጋብቻው ፡ የተገኙ ፡ መሆናቸውን ፡ ለማሳወቅ ፡ ይችላሉ ። ወይንም ፡ በፍ/ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፯፻፷፫ ፡ እና ፡ ፯፻፸፭(፩) ፡ መሠረት ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ የተወለዱ ፡ መሆናቸውን ፡ ሊያሳውቁ ፡ ይችላሉ ። የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ባለቤት ፡ የመጀመሪያውን ፡ አማራጭ ፡ ሃሳብ ፡ ይደግፋሉ ፤ ምክንያቱም ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻው ፡ እንኳን ፡ ክርክር ፡ ቢነጥመው ፡ የቀድሞው ፡ ሁኔታ ፡ ሕጋዊነት ፡ እርግጠኛ ፡ ስለሆነና ፡ የፍ/ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፯፻፷፫ ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነትን ፡ "አንድ ፡ ሰውና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ በሕግ ፡ በሚጸና ፡ እኳን ፡ ጋብቻ ፡ ሳያደርጉ ፡ እንደ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ሆነው ፡ በመኖር ፡ የሚገኘውን ፡ ሁኔታ ፡" ነው ፡ ብሎ ፡ ስለሚተረጉመው ፡ ነው ።

67. እሳይ ፡ በመግለጫ ፡ ቁ. ፴፮ ፡ የተመለከቱት ፡ እር ፡ ዳቪድ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ቁ. እንዲህ ፡ ይላል ፦ "በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ እንደማድረጉ ፡ ዓይነት ፡ ውጤት ፡ አለው ፡ ግንኙነቱ ፡ እንዳቆመ ፡ ዳኞቹ ፡ አዲሱ ፡ ተጋቢ ፡ ድርጊቱን ፡ የፈጸመው ፡ በቅን ፡ ልቡናው ፡ ከሆነ ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ ያደርጉለታል ።" በተጨማሪም ፡ በግርጌ ፡ መግለጫ ፡ ቁ. ፭፪ ፡ የሰፈረውን ፡ የጂ ፡ ቹቹኖቪች ፡ ጥያቄ ፡ ይመለከቷል ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ፫ ፤ (፲፱፻፷፬) ።

68. በለጥሻቸው ፡ በንቲ ፡ ከሳሽ ፤ ወ/ አረጋይ ፡ መገንታ ፡ ተከሳሽ ፡ (አ/አበባ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍ/ቤት ፤ የፍ/ብሔር ፡ ክስ ፡ ቁ. ፩ሺ፩፻፹፱/፷ (ታትሞ ፡ ያልወጣ) ።

69. የፍ/ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፴፮ ።

ጅማም ፡ ውስጥ ፡ ቡና ፡ ቤት ፡ ከፍታ ፡ ትንግድ ፡ ነበር ፡ የሚለውን ፡ ማስረጃ ፡ አልተቀበለውም ። እንዚህ ፡ ነገሮች ፡ ስለተፈጸሙ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ተፋቱ ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ፍ/ቤቱ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ፈረደ ።[70]

"የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፯፻፳፯ ፡ እና ፡ ተከታታይ ፡ ቁጥሮች ፡ እንደሚያስረዱት ፡ ሁሉ ፡ መፋታት ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ መጋባት ፡ አንዳንድ ፡ ሕጋዊ ፡ ሥርዓት ፡ መከተል ፡ አለበት ። ቁ. ፯፻፳፩(፪) "በዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ ላይ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አፈጻጸም ፡ መፋታትን ፡ ሊመወሰን ፡ አይቻልም" ፡ ይላል ። ከሳሿ ፡ ከሚቹ ፡ ባልዋ ፡ ጋር ፡ ያደረገችውን ፡ ጋብቻ ፡ ከማፍረሷ ፡ በፊት ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አግብታ ፡ ከሆነ ፡ ከሳሿ ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ በመፈጸምዋ ፡ ልትጠይቅበት ፡ ይገባል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁለተኛው ፡ ጋብቻ ፡ የቀድሞውን ፡ ሊሽር ፡ አይችልም ። በተጨማሪም ፡ የፍ/ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፭፻፹፭ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ በጋብቻ ፡ የተሳሰረ ፡ ከሆነ ፡ ጋብቻው ፡ እስከሚቆይ ፡ ድረስ ፡ ሁለተኛ ፡ ጋብቻ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ፡ ይላል ። ከሳሿ ፡ ቡና ፡ ቤት ፡ ከፍታ ፡ ንግድ ፡ ስለጀመረች ፡ የፍች ፡ ሥርዓት ፡ ፈጽማለች ፡ እንደማይባል ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ማስረጃም ፡ ሊቆጠር ፡ አይችልም ። ድርጊቱ ፡ አሳፋሪና ፡ የኀብረት ፡ ሰብ ፡ ፀር ፡ መሆኑ ፡ ግን ፡ አይካድም ። ከሳሿ ፡ ፊት ፡ ነኝ ፡ ብላ ፡ ለውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ የጻፈችው ፡ ጽሑፍ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ እንደመፋታት ፡ አይቆጠርም ። ይህም ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፡ ሚስት ፡ ባልዋን ፡ ወይም ፡ ባል ፡ ሚስቱን ፡ አልፈልግም ፡ ማለትን ፡ ሕግ ፡ ስለማይፈቅድ ፡ ነው ። እንዲያውም ፡ በፍ/ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፯፻፳፩(፩) መሠረት ፡ በባልና ፡ ሚስት ፡ መሃከል ፡ የሚደረግ ፡ መፋታት ፡ በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ ካልተፈጸመ ፡ በስተቀር ፡ አይፈቀድም ፡ ይላል ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ምክንያቶች ፡ ከሳሿ ፡ ባልዋ ፡ እስከሞተ ፡ ድረስ ፡ ሕጋዊ ፡ ሚስቱ ፡ ነበረች ። አንዳችም ፡ ሕጋዊ ፡ መፋታት ፡ አልተከናወነም ።"

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሳሿ ፡ የሚቹ ፡ ሕጋዊ ፡ ሚስት ፡ መሆንዋን ፡ አውቆላት ፡ የሚቹን ፡ ንብረት ፡ ለመካፈል ፡ እንዲያስችላት ፡ ማመልከቻ ፡ እንድታቀርብ ፡ ፈቅዶላታል ።

ይግባኙ ፡ ወደ ፡ ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡[71] በቀረበ ፡ ጊዜ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሳሿ ፡ (የአሁኗ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡)[72]

"የትዳር ፡ ቤቷን ፡ ትታ ፡ እንደሴተኛ ፡ አዳሪ ፡ በመኖር ፤ ፊት ፡ ነኝ ፡ ብላ ፡ ፈቃድ ፡ ለማግኘት ፡ ማመልከቷ ፤ በሰፈሯም ፡ ውስጥ ፡ በየእድሩና ፡ በየለቅሶው ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ ነኝ ፡ በማለቷና ፡ የባሏን ፡ የጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ባለመቃወሟ ፡"

የሚቹ ፡ ሕጋዊ ፡ ባለቤት ፡ ሆና ፡ ልትቆጠር ፡ አትችልም ፡ ሲል ፡ ወስኗል ። የከፍተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ በሚያጠናበት ፡ ጊዜ ፤ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲያትት ፡ የከሳሿ ፡ ማስረጃ ፡

"የእሷን ፡ አለመፋታትና ፡ ከሚቹ ፡ ጋር ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞቱ ፡ ድረስ ፡ አብረው ፡ መኖራቸውን ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ አያረጋግጥም ። ጋብቻና ፡ ፍቺ ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንዳላቸው ፡ ግልጥ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መታወቅ ፡ ያለበት ፡ በሕጉም ፡ መሠረት ፡ እንደሆን ፡ ፍቺውን ፡ የሚወስን ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ ፍቺው ፡ በአካባቢው ፡ ማስረጃ ፡ ሊረጋገጥ ፡ ይችላል ። የመልስ ፡

70. የተተረጐመው ፡ በአቶ ፡ እየነው ፡ ዋሴ ፡ ነው ።
71. የወለተ ፡ አረጋይ ፡ መገንተና ፡ የበለጥሻቸው ፡ በንቲ ፡ ጉዳይ ፤ (ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፷፱/፷፱) ፡ ያልታተመ ።
72. ትርጉም ፡ በአቶ ፡ አስፋው ፡ ሰይፈ ።

ሰጪዋን ፡ ኑሮ ፤ ጠባይና ፤ ድርጊት ፡ ስንመለከት ፡ በሕጋዊ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ፍቺ ፡ አልነበረም ፡ ብሎ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠው ፡ ሐተታ ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ አላገኘነውም ። ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተከሳሿ ፡ (የአሁኗ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡) ከሚች ፡ ጋር ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. መጋባቷን ፡ አይቶ ፡ ሕጋዊ ፡ ሚስት ፡ ናት ፡ ብሎ ፡ ወሰነ ፡”

ተገቢው ፡ ክብራቸው ፡ ሳይዘነጋ ፡ ሁለቱም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ተሳስተዋል ። ሁለቱም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ልትኖር ፡ የምትችለው ፡ አንድ ፡ ሕጋዊ ፡ ሚስት ፡ ብቻ ፡ ናት ፡ የሚለውን ፡ አስተሳሰብ ፡ ተቀብለዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ የመጀመሪያው ፡ ጋብቻ ፡ አልፈረሰም ፡ የሚለው ፡ የከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አስተሳሰብ ፡ ተቀባይነት ፡ ካገኘ ፡ እንግዲያው ፡ ሁለተኛው ፡ ጋብቻ ፡ ተቃውሞ ፡ ስላልቀረበበት ፡ በግምት ፡ እንደጸደቀ ፡ ስለሚቆጠር ፡ እሱም ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ጋብቻ ፡ ነው ። ሦስት ፡ ዓይነት ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሲኖሩ ፤ የጋብቻ ፡ ሕግ ፡ በመጣሱ ፡ ምክንያት ፡ ጋብቻ ፡ ሲፈርስ ፡ ይህ ፡ አንዱ ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።[73] ሁለቱም ፡ ጋብቻዎች ፡ በሞት ፡ ምክንያት ፡ ስለፈረሱ ፤ ሁለቱም ፡ ሚስቶች ፡ እኩል ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ሊጠይቁ ፡ ይችላሉ ።[74] ምንም ፡ እንኳን ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ የፈጸመው ፡ ሲሞት ፡ የመጀመሪያዋ ፡ ሚስት ፡ ሁለተኛውን ፡ ጋብቻ ፡ ለመቃረን ፡ ብትችልም ፤ የጋብቻ ፡ ሕግ ፡ በመጣሱ ፡ ምክንያት ፡ የጋብቻው ፡ መፍረስ ፡ ሁለተኛዋ ፡ ሚስት ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ እንድታገኝ ፡ ያደርግላታል ።[75] ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ከተጋቢዎቹ ፡ አንዱ ፡ ከሞተች ፡ በኋላ ፡ የጋብቻ ፡ ሕግ ፡ በመጣሱ ፡ ምክንያት ጋብቻ ፡ እንዲፈርስ ፡ ማመልከቻ ፡ ማቅረብ ፡ መቻሉ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ። በሕጉ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፲፫ ፡ መሠረት ፡ የመጀመሪያዋ ፡ ተጋቢ ፡ ከሞተች ፡ ሁለተኛው ፡ ጋብቻ ፡ ሕጋዊ ፡ ይሆናል ፤ ባጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ የፈጸመው ፡ ወይም ፡ ሁለተኛዋ ፡ ከሞተች ፡ ሁለተኛው ፡ ጋብቻ ፡ በሞቱ ፡ ምክንያት ፡ ይፈርሳል ። የፖላንድ ፡ ሕግ ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ የፈጸመው ፡ ሲሞት ፤ ጋብቻውን ፡ ስለማውደቅ ፡ ጉዳይ ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ያደርጋል ።[76] በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉም ፡ እኩል ፡ ይታያሉ ፡ እንጂ ፡ እንደዚያ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ አያደርግም ።

ከጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቅር ፡ የሚያሰኘው ፡ ከሳሹዋ ፡ እራሱዋ ፡ አለመፋታቷን ፡ እንድታረጋግጥ ፡ መደረጉ ፡ ነው ፤ ከሁኔታው ፡ ጋር ፡ ሲታይ ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ የማይቻል ፡ ነው ።[77] ይህም ፡ ውሳኔ ፡ “ጋብቻው ፡ አይጸናም ፡ ወይም ፡ ፈርሶአል ፡ የሚለው ፡ ተከራካሪ ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ፡” ከሚለው ፡ ከሕጉ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፯ ፡ ጋር ፡ አይስማማም ።

አሁን ፡ የሚሰጠው ፡ አስተያየት ፡ በጣም ፡ የሚያስደንቅ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ሁለት ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ የፈጸመ ፡ ሰው ፡ ተጋቢ ፡ ነን ፡ ሊሉ ፡ ይችላሉ ። ሁለት ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ተጋቢዎች ፡

---

73. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፷፫ ።

74. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፺፱ ።

75. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፸፮ ።

76. “ዘ ፡ ፖሊሽ ፡ ፋሚሊ ፡ ኤንድ ፡ ጋርዲያንሺፕ ፡ ኮድ” ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ፳፰ ፤ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰ ።

77. ምንም ፡ እንኳን ፡ ለወደፊት ፡ የጋብቻ ፡ ምዝገባ ፡ እንዲኖር ፡ የታሰበ ፡ ቢሆንም ፤ ፍቺም ፡ እንዲታወቅ ፡ ካልተደረገ ፡ ጥቅሙ ፡ የተወሰነ ፡ ይሆናል ። አር ፡ ዴቪድ ፡ በማስታወሻ ፡ ፳፮ ፡ ገጽ ፡ ፶፫ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ተመልከት ።

የጋራ ፡ ሀብት ፡ ተካፋዮች ፡ ነን ፡ ሊሉ ፡ ይችላሉ ። የማይችሉበትስ ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ አለ? የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ከሚስትም ፡ ሆነ ፡ ከአባትዬው ፡ ዕቁባት ፡ ለተወለዱ ፡ ልጆች ፡ መብት ፡ ለጋሥና ፡ የላላ ፡ አቋም ፡ አለው ።[78] ከጋብቻ ፡ የተወለዱ ፡ ልጆች ፡ ከጋብቻ ፡ ካልተወለዱ ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ መካፈል ፡ አለባቸው ። ይኸስ ፡ ጉዳይ ፡ በሚስቶች ፡ መካከል ፡ ለምን ፡ አይፈጸምም? ሕጉን ፡ አርቃቂው ፡ እንዳሰበው ፡ ሁሉ ፤ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ የሚፈጸም ፡ ጋብቻ ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የሚደረግ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ተቃውሞ ፡ ይደረግ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ለዚህ ፡ ተቃውሞና ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ጋብቻ ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ የለውም ፡ ለሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ ከተፈለገ ፡ ስለሕጋዊ ፡ ያልሆኑ ፡ ጋብቻዎች ፡ መፍረስ ፡ የሚያትቱትን ፡ ሕጎች ፡ መመልከት ፡ በቂ ፡ ነው ። ሕጋዊ ፡ ስላልሆን ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስና ፡ ፍቺ ፡ በብዙ ፡ ተመሳሳይ ፡ ሲሆኑ ፡ ውጤታቸውም ፡ አንድ ፡ ነው ።[79] ጋብቻው ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ የጸደቀ ፡ ጋብቻ ፡ ነው ። ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የተደረገ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ማለቅ ፡ ግን ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ነው ። የጋራ ፡ ሀብት ፡ አልተፈጠረም ፤[80] ቢበዛ ፡ ሴትዮዋ ፡ ለስድስት ፡ ወር ፡ መኖሪያ ፡ የሚበቃ ፡ ገንዘብ ፡ ታገኛለች ።[81]

ለዚህ ፡ ውሳኔ ፡ ሁለት ፡ ትልቅ ፡ ተቃውሞዎች ፡ ሊቀርቡ ፡ ይችላሉ ። በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ በፈጸመው ፡ ሰው ፡ ተጋቢዎች ፡ መሐከል ፡ የጋራ ፡ ሀብትና ፡ የጡረታ ፡ አበል ፡ የማከፋፈሉ ፡ አድራጎት ፡ ከባድ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። አንድ ፡ ሀብት ፡ የጋራ ፡ መሆን ፡ የሚጀምረው ፡ ከጋብቻው ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ስለሆነ ፤[82] ሀብቱም ፡ መካፈል ፡ ያለበት ፡ እንደ ፡ ጋብቻው ፡ ርዝመት ፡ መሆን ፡ አለበት ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ችግሮችና ፡ ክርክሮች ፡ ሊፈጠሩ ፡ ይችላሉ ። የበለጠ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ንብረት ፡ ከመቼ ፡ ጀምሮ ፡ እንደነበረና ፡ እንዲሁም ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ሊነሳ ፡ እንደሚችል ፡ ማንም ፡ ሊገምት ፡ ይችላል ። ጋብቻው ፡ በገንዘብ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ውጤት ፡ የሚለው ፡ የሕጉ ፡ ክፍልም ፡ ሲረቅ ፡ ይኸ ፡ ሁኔታ ፡ ይፈጠራል ፡ ተብሎ ፡ የተገመተ ፡ አይመስልም ። ሁለተኛው ፡ ተቃውሞ ፡ ደግሞ ፡ በሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፶፩ ፡ መሠረት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ የሚደረግን ፡ ጋብቻ ፡ ፈጽሞ ፡ ይቃረናል ፡ የሚለው ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ጋብቻ ፡ እንዳለ ፡ ተገንዝቦ ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ጋብቻ ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ ከሚደረግ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ አቋም ፡ እንዲኖረው ፡ ቢጥርም ፤[83] ይህ ፡ ሁኔታ ፡ በሕግ ፡ አውጪው ፡ ኮሚሲዮን ፡ ውድቅ ፡ ሆነ ፤ ይኸም ፡ የሆነው ፡ ምናልባት ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ የሚደረግን ፡

78. ፀሐፊዋ ፡ ግን ፡ ሕጋዊ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ የማይቆጠር ፡ ልጅ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የለም ከሚባለው ፡ አስተያየት ፡ ጋር ፡ አትስማማም ። የሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፷፭ (፫) ግልጥ ፡ እርጎ ፡ ከሕጋዊ ፡ ግንኙነቶች ፡ ውጭ ፡ ማለት ፡ ከጋብቻና ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በሚደረግ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ከሚኖሩ ፡ የሚወለዱ ፡ ልጆች ፡ ጉዲፈቻ ፡ ካልተሰጡ ፡ ወይም ፡ ልጆቼ ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ ተቀባይ ፡ ካላገኙ ፡ ከእናታቸው ፡ በስተቀር ፡ ከሌላ ፡ ጋር ፡ ሕጋዊ ፡ ግንኙነት ፡ የላቸውም ፡ ይላል ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፷ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ልጅነቱን ፡ በልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ ምክንያት ፡ ሊያረጋግጥ ፡ ይችላል ። ስለ ፡ ልጅነት ፡ ማረጋገጥ ፡ በጂ. ቼችኖቪች ፡ "ዘ ፡ ሎው ፡ ፊሊዬሽን ፡ አንደር ፡ ዘ ፡ ሲቪል ፡ ኮድ ፡" በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፤ ሦስተኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፶፯ ፡ እ. ኢ. አ.) ገጽ ፡ ፩፻፲፩ ፡ ተመልከት ።

79. ከላይ ፡ ገጽ ፡ ፲፬ ፡ ተመልከት ።

80. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፲፪ ።

81. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፲፯(፩) ፡ የአማርኛው ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የሚለው ፡ "ሦስት ፡ ወር" ፡ ነው ።

83. አር ፡ ዴቪድ ፡ ከላይ ፡ ማስታወሻ ፡ ፲፯ ፡ ገጽ ፡ ፶፰ ፡ የተጠቀሰ ።

ጋብቻ ፡ ሳለመፍቀድ ፡ የተደረገ ፡ ይሆናል ። ነገሩም ፡ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ የመጨረሻው ፡ ሀሳብ ፡ ወይም ፡ ሁኔታ ፡ ከፊተኛው ፡ የባሰ ፡ መጥፎ ፡ ነው ።[84]

## IV

## ፈጽሞ ፈራሽ ፡ የሆነ ፡ ጋብቻ ።

ፈራሽ ፡ የሆነ ፡ ጋብቻ ፡ የሚባለው ፡ የሕግ ፡ አረተሳሰብ ፡ በአብዛኛዎች ፡ የሕግ ፡ ስልቶች ፡ ውስጥ ፡ በአጠቃላይ ፡ አነጋገር ፡ ከመጀመሪያው ፡ ያልተፀነስ ፡ ወይም ፡ የሌለ ፡ ጋብቻ ፡ በመባል ፡ ይታወቃል ። ያልተፀነስ ፡ ጋብቻም ፡ በሕግ ፡ ዘንድ ፡ ፈራሽ ፡ እንደ ሆነ ፡ ጋብቻ ፡ ሁሉ ፡ ውጤተቢስ ፡ ነው ። ሁለቱም ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነቶች ፡ ውድቅ ፡ መሆናቸውን ፡ ለማሳወቅ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔን ፡ መጠየቅ ፡ አያሻም ። ምክንያቱም ፡ እነዚህ ፡ ዓይነቶቹ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ፈራሾች ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደተነገረው ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ እንዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻዎች ፡ ከመጀመሪያውኑ ፡ ያልተፀነሱ ፡ መሆናቸውን ፡ አስረድቶ ፡ ይኸው ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲረጋገጥ ፡ ማድረግ ፡ ይቻላል ።[85] በሕግ ፡ ፊት ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ፈራሽ ፡ በሆነው ፡ ስምምነትና ፡ ሳይፀነስ ፡ በቀረው ፡ ጋብቻ ፡ መካከል ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ልዩነት ፡ የለም ፡ በሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ ላይ ፡ ሁሉም ፡ ጸሐፊዎች ፡ ከስምምነት ፡ ላይ ፡ አልደረሱም ። ብዙ ፡ ጸሐፊዎች ፡ እንደሚሉት ፡ ከመሠረቱ ፡ ፈራሽ ፡ በሆነውና ፡ በተከታታይ ፡ በሕግ ፡ ሊፈርስ ፡ በሚችለው ፡ ጋብቻ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ በፈረንሣይ ፤ በስዊዘርላንድ ፡ እና ፡ በጀርመን ፡ ሕግ ፡ በተለያዩ ፡ ስሞች ፡ ቢታወቅም ፡ ሃሳቡ ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ።[86] ነገር ፡ ግን ፡ በትክክለኛው ፡ አስተሳሰብ ፡ ከተሄደ ፡ ፈራሽ ፡ የሆነ ፡ ጋብቻ ፡ ፈጽሞ ፡ ጋብቻ ፡ ተብሎ ፡ ሊጠራ ፡ አይችልም ።[87]

---

84. የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻን ፡ ጉዳይ ፡ ከመስማት ፡ ያፈገፍጋሉ ። በአዲስ ፡ አበባ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሦስት ፡ የወንጀል ፡ ክሶች ፡ የጥፋተኝነት ፡ ውሳኔ ፡ አልተሰጠባቸውም ። በወንጀል ፡ ቁጥር ፡ ፻፶፱/፷፩ ፡ (ያልታተመ ፡) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመጀመሪያው ፡ ጋብቻ ፡ ስለመደረጉ ፡ ማስረጃ ፡ የለም ፡ ብሏል ። በወንጀል ፡ ቁጥር ፡ ፴/፷፪ ፡ (ያልታተመ) ፡ የመጀመሪያዋ ፡ ሚስት ፡ ነገሩን ፡ ካነሳች ፡ በኋላ ፡ ተወች ። በወንጀል ፡ ቁጥር ፡ ፻፲፰/፷፩ ፡ (ያልታተመ) ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፳ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ ምክንያት ፡ አቤቱታውን ፡ ይከለክላል ፡ ብሎ ፡ በስሕተት ፡ ወሰነ ። ነገር ፡ ግን ፡ በአቃቤ ፡ ሕግና ፡ በኃይሉ ፡ ተ/መድህን ፡ ጉዳይ ፡ (ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀል ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፻፸፱/፶፱ ፡ (ያልታተመ) ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ምክንያት ፡ የተወሰነው ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ እሥራት ፡ ውሳኔ ፡ ፀድቋል ።

85. የፈረንሣይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከመታወጁ ፡ በፊት ፡ ትሮንች ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ፤ "ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ የሚባል ፡ ጋብቻ ፡ የለም ፡" ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ በሕግ ፡ እስከሚወሰን ፡ ድረስ ፡ የጋብቻን ፡ መኖር ፡ የሚያመለክት ፡ ሁኔታ ፡ ይኖራል ። "፩ ፡ ፱ኛ ፡ ገጽ ፡ ፶፫ ፡ ኤም ፡ ፕላኖይልና ፡ ጂ ፡ ሪፐርት ፡ እንደጠቀሱት ፤ ከላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ በቁ. ፳፬ ፡ ተጠቅሶአል ፤ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ቁጥር ፡ ፻፲፯፬።

86. ዲ ፡ ላሶክ ፤ ከላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፭ ፡ ተጠቅሶአል ፤ ገጽ ፡ ፶፫ ፡ ኢ. ጂ. ፡ ኮሀን ፤ የጋብቻ ፡ ፈራሽነት ፡ ሲ. ካርት ፤ ቮልዩም ፡ ፳፬ ፡ (፲፱፻፵፰) ፡ ገጽ ፡ ፫፻፳፱ ፡ ስለጋብቻ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ደረጃ ፡ መፍረስ ፡ የሚነገረው ፡ ልዩነት ፡ የተመሠረተው ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ በሳለው ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ነው ። ሌላው ፡ ዓይነት ፡ ልዩነት ፡ ደግሞ ፡ በውጤቱ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ። ይህም ፡ አንደኛው ፡ የመፍረሱ ፡ ውጤት ፡ ወደኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ለውጥ ፡ የሚያስከትል ፡ ሲሆን ፡ ሌላው ፡ ዓይነት ፡ የመፍረስ ፡ ውጤት ፡ ደግሞ ፡ እንደፍች ፡ ይቆጠራል ። ደብሊው ፡ ሙለር ፡ ፍሬንፍልስ ፤ የጀርመን ፡ የቤተሰብ ፡ ሕግና ፡ የውርስ ፡ ሕግ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ኤንድ ፡ ኮምፓራቲቭ ፡ ሎው ፡ ኳርተርሊ ፤ ቮሊዩም ፡ ፲፮ ፡ (፲፱፻፶፯) ገጽ ፡ ፬፻፴ ፤ ፬፻፴፪ ፡

87. የቤተክህነት ፡ ሕግና ፡ እራሱ ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ ባሳደሩት ፡ ተጽእኖ ፡ ምክንያት ፡ የእንግሊዝና ፡ የመሃል ፡ አውሮፓ ፡ ሕግ ፡ ጋብቻን ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ ችግር ፡ አጋጥሞአቸዋል ። ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ከእነዚህ ፡ አገሮች ፡ በቀሰመችው ፡ ትምህርት ፡ የተነሳ ፡ ከችግሩ ፡ ለመዳን ፡ በማሰብ ፡ ችግሩን ፡ በጥሩ ፡ ሁኔታ ፡ በማቃለል ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ እንዲኖር ፡ አድርጋለች ። ይህም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የሚታወቀው ፡ ሊፈርስ ፡ የሚችል ፡ ጋብቻ ፡ ነው ። ጋብቻው ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ ግን ፡ ከላይኛው ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ስለሆነ ፡ መናገር ፡ የማያሻው ፡ ጉዳይ ፡ ነው ።

"ያልተፀነሰ ፡ ጋብቻ ፡" የሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ አለ ። በጀርመን ፡ ሕግም ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ ምንም ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ ሊኖረው ፡ የማይችል ፡ በመባል ፡ ይታወቃል ። እንዲሁም ፡ በፖላንድ ፤ በጣሊያንና ፡ በስዊዘርላንድ ፡ ሕጎች ፡ "የሌለ ፡ ጋብቻ ፡" የሚል ፡ አስተሳሰብ ፡ አለ ።

"ሕጉ ፡ በግልጽ ፡ ጋብቻ ፡ አለመኖሩን ፡ በማያረጋግጥበት ፡ ጊዜና ፡ በሌላ ፡ በኩልም ፡ ደግሞ ፡ በትክክለኛ ፡ አስተሳሳብ ፡ ሲታይ ፡ የተደረገው ፡ ድርጊት ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ውጤት ፡ ይኖረዋል ፡ ብሎ ፡ ለማመን ፡ በማይቻልበት ፡ ጊዜ ፡"[88] ይህንን ፡ ሁኔታ ፡ የሚያጠቃልል ፡ ያልተፀነሰ ፡ ጋብቻ ፡ የሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ሥር ፡ እንዲሰድ ፡ ማድረግ ፡ ግድ ፡ ሆኖአል ። ይህ ፡ አስተሳሰብ ፡ በተለይም ፡ የጾታ ፡ ተመሳሳይነትና ፡ ልዩ ፡ የአሠራር ፡ ዘዴን ፡ የሚመለከቱ ፡ ጥያቄዎች ፡ በሚነሱበት ፡ ጊዜ ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ።[89] ፕላኖይል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ አሥራ ፡ ላይ ፡ ስለማዋል ፡ በከፊል ፡ ቢቃወምም ፡ "ፈጽሞ ፡ የጋብቻ ፡ መኖር ፡ ፍንጭ ፡ እንኳ ፡ የማይታይባቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ በሚያጋጥሙ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ አስተሳሰብ ፡ የሚያገፍ ፡ ይሆናል ፡" ሲል ፡ ጽፎአል ።[90] በፈረንሳይ ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ያልተፀነሰ ፡ ጋብቻ ፡ ስለሚባለው ፡ የሚደነገጉ ፡ የሕግ ፡ አንቀጾች ፡ የሉም ። ሃሳቡ ፡ ሊፈልቅ ፡ የቻለው ፡ ከጁሪስፕሩደንስ ፡ ነው ።

ከኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰለው ፡ የፖላንድ ፡ ሕግ ፡ ሊፈርስ ፡ የሚችል ፡ ጋብቻ ፡ እና ፡ ያልተደረገ ፡ ጋብቻ ፡ በማለት ፡ ልዩነት ፡ ያደርጋል ። በብሔራዊ ፡ የጋብቻ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አፈጻጸም ፡ መሠረት ፡ ሳይሆን ፡ ማለትም ፡ ጋብቻው ፡ የተፈጸመው ፡ በሃይማኖት ፡ የጋብቻ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ ሬጂስትራር ፡ ሳይኖርበት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ጋብቻው ፡ እንዳልተደረገ ፡ ይቆጠራል ። እንዲሁም ፡ ጾታቸው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ በመባባል ፡ የሚፈጽሙት ፡ የብሔራዊ ፡ ጋብቻ ፡ እንዳልተደረገ ፡ ጋብቻ ፡ መቆጠር ፡ ይኖርበታል ።[91]

ያልተደረገ ፡ ጋብቻ ፡ የሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ ያሉባቸው ፡ የሕግ ፡ ስልቶች ፡ ውስጥ፡ አፈጻጸሙ ፡ የብሔራዊ ፡ ጋብቻን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ያልተከተለ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ መሟላት ፡ ያለባቸው ፡ የአሠራር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሲጓደሉ ፡ የዚህ ፡ ውጤት ፡ ጋብቻው ፡ እንዳልተደረገ ፡ የሚያስቆጥረው ፡ ይሆናል ።[92] በኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ለየት ፡ ይላል ። ምክንያቱም ፡ የጋብቻ ፡ አፈጻጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መሟላትና ፡ አለመሟላት ፡ በሕጉ ፡ ዘንድ ፡ የተሰጠው ፡ ቦታ ፡ በጣም ፡ ዝቅተኛ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ስለብሔራዊ ፡ ጋብቻ ፡ አፈጻጸም ፡ ሃለፊ ፡ የሆነው ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ መፈጸም ፡ ያለበትን ፡ በሕግ ፡ የተደነገገውን ፡ ሳይፈጽም ፡ ቢቀር ፡ ባለሥልጣኑ ፡ በወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሚቀጣ ፡ ቢሆንም ፡ ጋብቻው ፡ ግን ፡ ሕጋዊ ፡ ሆኖ ፡ ይቀራል ።[93] እንዲሁም ፡ የሃይማኖት ፡ ጋብቻ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ ባለማሟላት ፡ ወይም ፡

---

88. ኤም. ፕላኖይል ፡ እና ፡ ጂ. ሪፐርት ፤ ትራታይዝ ፡ ኤን. ዘ. ሲቪል ፡ ሎው ፤ (፲፪ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፴፱) (በሊዊዚና ፡ ሴቴት ፡ ሎው ፡ እንስቲትዩት ፡ እንደተተረጐመ ፤ (፲፱፻፶፱) ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፩ ።

89. እዚያው ፡ ይመልከቱ ።

90. እዚያው ፡ ይመልከቱ ።

91. ዱ. ፡ ላሰክ ፤ ከላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፷፩ ፡ ተጠቅሶአል ፤ ገጽ ፡ ፶፫ ።

92. በፈረንሣይ ፤ በጀርመን ፤ በስዊዘርላንድ ፤ በፖላንድ ።

93. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፲፻፰፩ ፡ እና ፡ ፲፻፰፪ ፡ ሆኖም ፡ የዚሁ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፻፰፰ ፡ አተረጓጐም ፡ ጉዳይ ፡ የተሟላ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

በሌላ ፡ መሰናክል ፡ ምክንያት ፡ በሃይማኖት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ዘንድ ፡ የተነገረ ፡ የጋብቻ ፡ መሻር ፡ ለፍች ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ጋብቻው ፡ ተቀባይነት ፡ ይኖረዋል ።[94] በልማድ ፡ ጋብቻ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የተከናወነ ፡ የልማድ፡ ጋብቻ ፡ መሻር ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ተቀባይነት ፡ አያገኝም ።[95]

ተመሳሳይ ፡ ጾታ ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የተፈጸመ ፡ ጋብቻ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ዘንድ ፡ ፈራሽ ፡ ሳይሆን ፡ እንደማይቀር ፡ ይገመታል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ይህ ፡ የተጠቀሰው ፡ ጉዳይ ፡ ለመከራከሪያ ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ የሚያገለግል ፡ መስሎ ፡ ቢታይም ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጉዳዮች ፡ ሌሎችን ፡ አገሮች ፡ አጋጥመዋቸዋል ። ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ፕላኖይል ፡ ሲጽፍ ፤

"የፍርድ ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፡ ሲመረመሩ ፡ ችግሩ ፡ እርግጥ ፡ ሊደርስ ፡ እንደሚችል ፡ ያስረዳል ። አብረው ፡ ለመኖር ፡ በማሰብ ፡ በሚጣመሩት ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የጾታ ፡ ልዩነት ፡ እንዳለ ፡ በጋብቻ ፡ ዓይነተኛ ፡ ወግ ፡ መሆኑ ፡ አያከራክርም ። የተጋቢውን ፡ ወገን ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ስሕተት ፡ ሲደረግ ፤ ወይም ፡ ከሁለቱ ፡ አንዱ ፡ የተለየ ፡ ጾታ ፡ ሳይኖራቸው ፡ ሲቀር ፡ ጋብቻው ፡ ያለምንም ፡ ማመንታት ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ። የጾታው ፡ ነገር ፡ አሻሚ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ሌላው ፡ ይቅርና ፡ የጋብቻ ፡ መልክ ፡ የያዘ ፡ ፍንጭ ፡ እንኳ ፡ አይኖርም ።"[96]

አንድ ፡ በፈረንሣይ ፡ አገር ፡ የተደረገ ፡ ጋብቻ ፡ የወንድና ፡ የሴትን ፡ ግንኙነት ፡ ያልፈጠረ ፡ በመሆኑ ፡ ፈራሽ ፡ ሆኖአል ።[97] የጾታውን ፡ ጉዳይ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ለማድረግ ፡ ስላለመቻል ፡ ወይም ፡ ተገቢውን ፡ በሚመለከት ፡ ነገር ፡ ከሚደረገው ፡ መሳሳት ፡ ጋር ፡ አቀላቅሎ ፡ ለመረዳት ፡ መሞከር ፡ ስህተት ፡ ስለሆነ ፡ ስለልዩነቱ ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ።[98]

ምንም ፡ እንኳ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለጾታ ፡ መመሳሰል ፡ ጉዳዩ ፡ የሚወስን፡ መስሎ ፡ መታየቱ ፡ እውነት ፡ ቢሆንም ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ የዚሁ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ሲመረመር ፡ ይህ ፡ አለመሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ቁጥር ፡ ፭፻፶፮(ሐ)[99] እንደሚደነግገው ፡

---

94. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፲፻፷፫(፩) እና ፡ (፪)

95. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፲፻፷፫(፫)

96. ኤም ፡ ፕላኖይል ፡ እና ፡ ጂ. ሪፐርት ፡ ከላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁ. ፺፬ ፡ ተጠቅሶአል ። ቮልዩም ፡ ፪ ቁ. ፩፺፩ ።

97. የዳርቦስና ፡ ዳርቦስ ፡ ኩር ፡ ዱአፔል ፡ ሞንትፔሊር ፤ ፍራንስ ፤ ሜይ ፡ ፳ ፡ ፲፱፻፸፪ ፡ ዳሎዝ ፡ ፲፺፻፸፪ ፤ ክፍል ፡ ፪ ፡ ገጽ ፡ ፵፰ ፡ በተጠቀሰው ፡ ጉዳይ ፡ በሴትየዋ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ለመፈጸም ፡ የሚያስችል ፡ ከውስጣዊ ፡ አካሏ ፡ የሌለ ፡ በመሆኑ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሴት ፡ ናት ፡ ከማለት ፡ ይልቅ ፡ እንደ ፡ ወንድ ፡ የምትቆጠር ፡ ናት ፡ ሲል ፡ ወስኗል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲያትት ፡ ጋብቻ ፡ ሲባል ፡ አንድ ፡ ወንድና ፡ አንድ ፡ ሴት ፡ የሚዋሃዱበት ፡ ስለሆነ ፡ ሚስትየዋ ፡ ሴት ፡ በማትሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ይሆናል ፡ ብሏል ። የዚህን ፡ ተቃራኒ ፡ በዳም ፡ ጂ ፡ (ኩር ፡ ዶ ፡ ካሳሲዮ ፤ ፍራንስ ፤ ኤፕሪል ፡ ፯ ፡ ፲፱፻፫ ፡ (ዳሎዝ ፡ ፲፱ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፶፩ ፡)) ይመለከቷል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሰጠው ፡ ውሣኔ ፡ አንዳንድ ፡ የጾታ ፡ መጉደል ፡ ሲገኝ ፡ ሁኔታው ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ለመፈጸም ፡ አለመቻል ፡ ይባላል ፡ የሚል ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጋብቻ ፡ ሊደረግ ፡ የሚችለው ፡ በሁለት ፡ ተቃራኒ ፡ ጾታዎች ፡ መሆኑን ፡ ሳይክድ ፡ በቀረበለት ፡ ጉዳይ ፡ ግን ፡ ሚስትየዋ ፡ እንደሴት ፡ ትቆጠራለች ፡ ብሏል ።

98. የፈረንሣይ ፡ የሕግ ፡ ሊቆች ፡ ከሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ የመጉደል ፡ ጉዳይ ፡ ሰውየው ፡ ተቃራኒ ፡ ጾታ ፡ አለው ፡ እንደማያሰኘው ፡ ተስማምተዋል ። ከዚህ ፡ ሰየት ፡ ያለ ፡ በአካሉ ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ምልክት ፡ መታየት ፡ ይኖርበታል ።

99. ቁጥር ፡ ፭፻፶፮ ፡ ስሕተት ፡ ተሠርቷል ፡ የሚያሰኙትን ፡ ምክንያቶች ፡ በጠባቡ ፡ ወስኗቸዋል ። በቁጥር ፭፻፶፮ ፡ (ሐ) መሠረት ፡ ስሕተት ፡ አለ ፡ የሚባለው ፡ "በሚያገቡት ፡ ሰው ፡ ጤና ፡ ወይም ፡ ሰውነት ፡ መሳሳት ፡ ይኸውም ፡ ያገቡት ፡ ሰው ፡ ደዌ ፡ ሥጋ ፡ የያዘው ፡ ወይም ፡ የሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነትን ፡ ለመፈጸም ፡ የማይችል ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ።" "ይህም ፡ አውቆ ፡ ግንኙነት ፡ ሳለማድረግ ፡ እምቢ ፡ ማለትን ፡ አይመለከትም ፡ የአማርኛው ፡ ቅጅ ፡ ግን ፡ "የሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነትን ፡ ለመፈጸም ፡ የማይችል፡ ይላል ። ይህም ፡ የሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ መሞትን ፡ እና ፡ ምናልባትም ፡ እምቢተኛነትን ፡ ጭምር ፡ ያጠቃልላል ።

ስሕተት ፡ ተደርጓል ፡ የሚባለው ፡ ስለሚያገቡት ፡ ሰው ፡ "ሰውነት ፡ መሳሳት ፡" ማለ ትም ፡ ያገቡት ፡ ሰው ፡ "የሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ለመፈጸም ፡ የማይችል ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ" ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ የጋብቻ ፡ ውጤት ፡ የሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነትን ፡ በመ ፈጸም ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ባይሆንም ፡[100] በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ስሕተት ፡ ተደርጎ ፡ ያገ ባው ፡ ሰው ፡ ጋብቻውን ፡ የፈቀደው ፡ በስሕተት ፡ እንጂ ፡ እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ አውቆ ፡ ኑሮ ፡ ለጋብቻው ፡ ፈቃደኛ ፡ የማይሆን ፡ መሆኑን ፡ በማስረዳት ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ ጥያቄ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።[101] ነገር ፡ ግን ፡ ተጋቢዎቹ ፡ አንድ ፡ ዓይ ነት ፡ ጾታ ፡ ያላቸው ፡ ከሆነ ፡ ምንም ፡ ጋብቻ ፡ የለም ። በስሕተት ፡ ቢሆንም ፡ ባይሆንም፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጋብቻ ፡ ወዲያውኑ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።[102]

የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ሁኔታ ፡ ሲያጋጥም ፡ የጀርመን ፡ ሕግ ፡ ፈጽሞ ፡ ጋብቻ ፡ እንዳሌለ ፡ ይቆጥረዋል ።[103] ይህም ፡ ከመጀመሪያው ፡ ጀምሮ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ስምምነት ፡ ሳይኖር ፡ ሲቀር ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የዚህን ፡ ዓይነቱን ፡ ጋብቻ ፡ ፈራሽ ፡ እንደሚያደር ገው ፡ ይታመናል ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፹፯(፩) "እያንዳንዳቸው ፡[104] ተጋቢዎች ፡ ጋብቻ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ራሳቸው ፡ መፍቀድ ፡ አለባቸው ፡" በማ ለት ፡ ይደነግጋል ። ጋብቻን ፡ በወኪል ፡ ወይም ፡ በመልክተኛ ፡ መፈጸም ፡ አይቻልም ። ቀደም ፡ ብለን ፡ እንደተመለከትነው ፡ ስለፈቃደኛነት ፡ በምናወሳበት ፡ ጊዜ ፡ አብሮ ፡ የሚነሳው ፡ ጉዳይ ፡ በተለይም ፡ በችሎታ ፡ ማጣት ፡ በግዴታና ፡ በስሕተት ፡ ምክንያት ፡ ሊፈርስ ፡ ስለሚችል ፡ ጋብቻ ፡ ነው ። እነዚህን ፡ የተጠቀሱትን ፡ ሁሉ ፡ የሚመለከቱና ፡ ጋብቻን ፡ ለማፍረስ ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚያስችሉ ፡ አንቀጾች ፡ ተደንግገዋል ። ሆኖም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ለማግባት ፡ ምንም ፡ ሃሣብ ፡ ሳይኖረው ፡ ለምሳሌም ፡ ከተጋቢ ዎቹ ፡ አንደኛው ፡ ስለጋብቻው ፡ አፈጻጸም ፡ ምንም ፡ የሚያውቀው ፡ ነገር ፡ ሳይኖር ፡ ጋብቻው ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ የተደረገውን ፡ ጋብቻ ፡ ለማፍረስ ፡ የሚያስችል ፡ ሕግ ፡ የለም ።[105] ስለጋብቻው ፡ አፈጻጸም ፡ ያለማወቁም ፡ ነገር ፡ ሊፈጠር ፡ የሚችለው ፡ በመጠጥ ፡ ኃይል ፡ ወይም ፡ አእምሮ ፡ የሚያስት ፡ እጽ ፡ በመውሰድ ፡ የተነሳ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ጠቅላላ ፡ ስምምነት ፡ በማይገኝበትም ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ ሊገቡ ፡ የሚችሉ ፡ ሁኔ ታዎች ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ በጋብቻው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ አልፈልግም ፡ ሲል ፡

---

100. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ቁ. ፲፻፹፯ ፡ እንደሚያስረዳው ፡ "ጋብቻው ፡ ለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ የሩ ካቤ ፡ ሥጋው ፡ ግንኙነት ፡ በውነት ፡ መፈጸም ፡ ወይም ፡ በግምት ፡ ተፈጽሟል ፡ መባሉ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።"

101. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፳፻፲ ፡ እና ፡ ፲፻፲፰ ። በአንድ ፡ በፈረንሣይ ፡ አገር ፡ በተደረገ ፡ ክርክር ፡ የሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ መሞት ፡ የተጋቢውን ፡ ወገን ፡ ፈቃደኛ ፡ አለመሆን ፡ ስለሚያሳይ ፡ እንደ ፡ ስሕተት ፡ ይቆጠ ራል ፡ ተብሏል ።

102. ጋብቻው ፡ የጋብቻ ፡ መልክ ፡ እንኳ ፡ ስለማይኖረው ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ። የጋብቻ ፡ መልክ ፡ ካለማለትም ፡ ተጋቢዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ተቃራኒ ፡ ጾታ ፡ አላቸው ፡ የሚል ፡ ግምት ፡ ካለ ፡ ጋብቻው ፡ ፈራሽ ፡ አይሆንም ።

103. ኢ. ጂ. ኮኸን ፤ ማንዋል ፡ ኦፍ ፡ ጀርመን ፡ ሎው ፤ ፪ኛ ፡ እትም ፤ ለንደን ፤ ብርቲሽ ፤ ኢንስቲቲዩሽን ፡ ኦፍ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ኤንድ ፡ ኮምፓራቲቭ ፡ ሎው ፤ (፲፱፻፷፰) ቮልዩም ፡ ፩ ። ቁ. ፲፫፻፳ ፡ ደብሊው ፡ ሙለር ፡ ፍሬንፍልስ ፤ ከላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፹፪ ፡ ተጠቅሷል ፤ ገጽ ፡ ፴፻፹፩ ።

104. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፹፯(፪) ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፈቃድ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

105. የእነ ፡ ኬሊ ፡ ጉዳዩ ፡ (ከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ እንግ ፤ ፲፱፻፴፱) ፡ ቱሌን ፡ ሎው ፡ ሪቪው ፡ ቮልዩም ፡ ፲፭፬ ፡ ገጽ ፡ ፺፱ ፤ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ሙሽራይቱ ፡ የሠርጉ ፡ በዓል ፡ የቀሰበት ፡ በዓል ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ ተከራክረች ። የእንግሊዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ጋብቻው ፡ ከመሠረቱ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ወሰነ ። የእነ ፡ ቫልየር ፡ ጉዳይ፤ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንግ ፤ ፲፱፻፳፭ ፡) ኤል. ቲ. ቮልዩም ፡ ፻፴፫ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፴ ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የነበረው ፡ ሙሽራ ፡ የጋብቻው ፡ በዓል ፡ እየተከበረ ፡ መሆኑን ፡ በፍጹም ፡ አላወቅሁም ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ ተከራከረ ። ይህም ፡ ጋብቻ ፡ ከመሠረቱ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የእን ግሊዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወሰነ ።

ወይም ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ ሳይሰጥ ፡ ሲቀር ፡ ነው ። ለጋብቻ ፡ ስምምነትን ፡ የመስጠቱ ፡ ትርጉም ፡ ሊገባው ፡ የማይችል ፡ ሰው ፡ የሰጠውን ፡ ስምምነት ፡ ውድቅ ፡ የሚያደርግ ፡ አንቀጽ ፡ በመጨመር ፡ ሕግ ፡ አርቃቂው ፡ እላይ ፡ የተነገረውን ፡ ችግር ፡ ለማስወገድ ፡ አስቦ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ይህ ፡ አንቀጽ ፡ ሳይጨመር ፡ ቀርቷል ።[106]

ዋጋ ፡ የሌላቸው ፡ ጋብቻዎች ፡ ውጤት ፡ እላይ ፡ ተዘርዝረዋል ። ጋብቻ ፡ ስለ ሌለ ፡ ውጤቶችም ፡ ሊኖሩ ፡ አይችሉም ።

ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ጋብቻ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ ከመዋሉ ፡ በፊት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚታወቅ ነገር ፡ ነበር ። ለአዲስ ፡ አበባ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡[107] በቀረበ ፡ አንድ ፡ ክስ ፡ ጋብቻው ፡ ከመጀመሪያው ፡ ፈጽሞ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ተወስኗል ። ለክሱ ፡ መነሻ ፡ የሆኑት ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ የሚከተሉት ፡ ነበሩ ። ተጋቢዎቹ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ብሔራዊ ፡ ጋብቻቸውን ፡ አከበሩ ። እነዚህ ፡ ሁለት ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ የተዋወቁት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ውጭ ፡ ነበር ። ከተዋወቁም ፡ በኋላ ፡ እንዲጋቡ ፡ በደብዳቤ ፡ ተስማሙ ። የአሁኗ ፡ መልስ ፡ ሰጪ ፡ የወደፊት ፡ ባሏ ፡ የሚሠራው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ስለነበረ ፡ ጋብቻውን ፡ ሊመፈጸም ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጣች ። እንደ ፡ ደረሰችም ፡ ብዙ ፡ የመንፈስ ፡ መወራጨት ፡ ታየባት ፤ በመጀመሪያ ፡ ጋብቻውን ፡ አልፈልግም ፡ አለች ። ሆኖም ፡ በነበረችበት ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያትና ፡ በወዳጆች ፡ ገፋፊነት ፡ ከሳሹን ፡ አገባች ። በሚጉላው ፡ ጊዜ ፡ ጋብቻው ፡ በሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ እንዳይፈጸም ፡ እንቢ ፡ አለች ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ጋብቻው ፡ በሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ አልተፈጸመም ። ከሦስት ፡ ሳምንት ፡ በኋላ ፡ ሙፋታቷን ፡ የሚገልጽ ፡ ደብዳቤ ፡ ለኤምባሲዋ ፡ ትታ ፡ ሐገሪቷን ፡ ለቃ ፡ ሄደች ።

"በጋብቻው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጊዜ ፡ ተከሳሽ ፡ ጋብቻውን ፡ በሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ የመፈጸም ፡ ዓላማ ፡ አልነበራትም ፤ ይኸም ፡ ስለሆነ ፡ ለጋብቻ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆኑት ፡ አንደኛው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ አልተሟላም ፡" በማለት ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጋብቻው ፡ ከመጀመሪያው ፡ ፈጽሞ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ወስኗል ።

ይህ ፡ ክስ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ቢነሳ ፡ ለጉዳዩ ፡ መፍትሔ ፡ ለማግኘት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ ሕግ ፡ መመልከት ፡ ይኖርበት ፡ ነበር ። የሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ በጋብቻ ፡ ውጤቶች ፡ ላይ ፡ ዋጋ ፡ ስለማይኖርው ፡[108] እንዲሁም ፡ ይህ ፡ ክስ ፡ የቀረበው ፡ ጋብቻውን ፡ በሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ለመፈጸም ፡ ባለመቻል ፡ ሳይሆን ፡ አውቃ ፡ ስላልፈለገች ፡ ስለሆነ ፡[109] ጋብቻውን ፡ የሚያፈርስ ፡ አንቀጽ ፡ ባለመኖሩ ፡ ምክንያት ፡ ጋብ

---

106. ዳቪድ ፤ እላይ ፡ በተራ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፺፯ ፤ መግለጫ ፡ ፳፩ ። እንዲሁም ፡ ቹቹኖቪችን ፡ ተመልከት ፤ እላይ ፡ በተራ ፡ ቁጥር ፡ ፶፬ ፡ የተጠቀሰው ፡ ፕሮብሌም ፡ ፴፯ ፡ "ጥያቄዎች ፡" የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፤ ፬ልዩም ፡ ፰ ፤ (፲፱፻፷፱) ።

107. ከማሽ ፡ ቶርሰን ፤ ተከሳሽ ፡ ግሬይሰን ፤ (የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱፩/፶፩ ፤ የንግድ ፡ ችሎት ፡) (ያልታተመ ።)

108. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፲፻፭፺ ፤ የሚለው ፡ እላይ ፡ በተራ ፡ ቁጥር ፡ ፲ ፡ ተሰጥቷል ።

109. እሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ የመፈጸሚያ ፡ ብልቶች ፡ በመጓደላቸው ፡ ምክንያት ፡ ጋብቻን ፡ በሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ለመፈጸም ፡ አለመቻልን ፡ የሚመለከተው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፺፩(ሐ) ፡ ነው ። ይኸውም ፡ አንቀጽ ፡ ስለጉድለቱ ፡ ስሀተት ፡ መደረጉንም ፡ ይመለከታል ። አንቀጹ ፡ የሚለው ፡ እላይ ፡ በተራ ፡ ቁጥር ፡ ፶፱ ፡ ተሰጥቷል ። ባለቤትየው ፡ ወይም ፡ ባለቤትየዋ ፡ ጋብቻውን ፡ በሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ሲፈጽሙ ፡ እየቻሉ ፡ ፈቃደኞች ፡ በማይሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ መደረግ ፡ የአለበት ፡ በቀጥታ ፡ አልተነገረም ፤ ሆኖም ፡ አማርኛው ፡ የሚለው ፡ የሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ለመፈጸም ፡ አለመቻል ፡ ስለሆነ ፡ ፈቃደኛ ፡ አለመሆንም ፤ አለመቻል ፡ ነው ፤ ተብሎ ፡ ሊተረጐም ፡ ይቻላል ። ቹቹኖቪችን ፡ ተመልከት ፤ እላይ ፡ በተራ ፡ ቁጥር ፡ ፶፬ ፡ ተጠቅሶአል ፤ ፕሮብሌም ፡ ፰ ፤ እና ፡ "ጥያቄዎች" ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፤ ፬ልዩም ፡ ፰ ፤ (፲፱፻፷፱) ።

ቻው ፣ ምናልባት ፣ ሕጋዊ ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ በስተቀር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ መፍትሔ ፡ አያገኝለትም ። እንደዚህ ፡ ከሆነም ፡ ጋብቻው ፡ ሊፈርስ ፡ የሚችለው ፡ በመፋታት ፡ ነው ። ሆኖም ፡ የመጋባት ፡ አላማ ፡ ስለሌለ ፡ ጋብቻው ፡ ከመጀመሪያውም ፡ ፈጽሞ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ። ሆኖም ፤ የጋብቻ ፡ ስምምነት ፡ ፈጽሞ ፡ አልነበረም ፡ ለማለት ፡ የሚያስችል ፡ መሆን ፡ አለበት ።

## V

## መደምደሚያ ።

በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የተጠቀሱት ፡ ሊፈርሱ ፡ የሚችሉ ፡ ጋብቻዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። አንድ ፡ ጋብቻ ፡ ጉድለት ፡ ሲኖረው ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የሚቀር ፡ ሲሆን ፤ ጋብቻው ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ሆኖም ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ እስኪደረግ ፡ ድረስ ፡ ወይም ፡ ካልፈረሰ ፡ በስተቀር ፡ እንደዚህ ፡ ዐይነቱ ፡ ጋብቻ ፡ ቋሚ ፡ ነው ። እንዲፈርስ ፡ ከተደረገ ፡ ግን ፡ ከፈረሰበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ውጤት ፡ አይኖረውም ፤ ሆኖም ፡ አስቀድሞ ፡ የነበሩት ፡ ውጤቶች ፡ የተጠበቁ ፡ ይሆናሉ ። የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ የወደፊቱን ፡ ብቻ ፡ የሚመለከት ፡ ነው ።

ከመጀመሪያው ፡ ፈጽሞ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸው ፡ ጋብቻዎች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ በግልጽ ፡ አልተጠቀሱም ። አንድ ፡ መሠረታዊ ፡ ጉድለት ፡ በመኖሩ ፡ ምክንያት ፡ ጋብቻው ፡ ከመጀመሪያው ፡ ፈጽሞ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ ጋብቻ ፡ የማይኖርበትን ፡ ሁኔታ ፡ የሚመለከት ፡ ሕግ ፡ መጨመሩ ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሕግ ፡ የጋብቻው ፡ ዓላማ ፡ ወይም ፡ ጠባይ ፡ በሚናጋበት ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ መወሰን ፡ አለበት ። ለዚህም ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆነው ፡ የመጋባት ፡ ስምምነት ፡ በሌለበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ጋብቻው ፡ የጋብቻን ፡ መልክ ፡ በማይዝበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ከመጀመሪያው ፡ ፈጽሞ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ጋብቻ ፡ የሚያስከትላቸው ፡ ውጤቶች ፡ ሊኖሩ ፡ አይችሉም ።

ጉድለት ፡ የአለባቸውን ፡ ጋብቻዎች ፡ የሚመለከት ፡ ሕግ ፡ በእነዚህ ፡ ሁለት ፡ ሁኔታዎች ፡ መወሰን ፡ አለበት ። ሊፈርስ ፡ የሚችለውን ፡ ጋብቻ ፡ ወደኋላ ፡ በመመለስ ፡ ለማፍረስ ፡ እንዲቻል ፡ ከመጀመሪያውኑ ፡ ፈጽሞ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ የሚያስፈልግበት ፡ ምንም ፡ ምክንያት ፡ አይኖርም ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ጋብቻ ፡ የሰውን ፡ መብቶች ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ይጥላል ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ተፈላጊነት ፡ የለውም ።